## ፅንፈኝነትና የአማራው እልቂት
ገጽ 9

## የደም ፖለቲካው ማዕከል፡- ወልቃይት
ገጽ

# ባልደራስ

1ኛ ዓመት ቁጥር 04 ታህሳሥ 10 ቀን 2013 ዓ.ም.



# ውስጠ ወይራው ያለመለወጥ 'ለውጥ'

## ኦነግ በወለጋ ወደ 60 አማራዎችን ገደለ የ3ቱን ምላስ ቆርጧል
ገጽ 3

## ከመንግሥት ያፈነገጡ የመከላከያ አባላት ከፊል የትሕነግ መሪዎችን ጫካ ውስጥ አገቱ
ገጽ 3

## አባ ገዳዎች በደራ ቡድን ለመመሥረት እንቅስቃሴ ጀመሩ
ገጽ 3

# መንግሥታዊ አላጋጭነት ይቁም !

ሰሞኑን ወጉ እንዳይቀር ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀን ተከብሮ አልፏል:: በአሉ የተከበረው በፖለቲካና በህሊና እስረኞች ላይ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እየተፈፀመበት ባለው በቃሊቲ ወህኒ ቤት ጭምር መሆኑ ሳያንስ የአብይ አሕመድ አገዛዝ ራሱ ጨቋኝ ራሱ የመብት አከባሪ ሆኖ መምጣቱ ነውሩን አያውቅ ባለጌ ኑግ በልቶ ይስቃል ያስብላል:: ይህ ቀን በተከበረበት ጊዜ የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች አቶ ስንታየሁ ቸኮልና ወይዘሮ አስቴር ስዩም ህክምና ተከልክለው በከፍተኛ ህመም ላይ ነበሩ:: አቶ ስንታየሁ የኩላሊት ሕመም ስላጋጠማቸው በፖሊስ ሀኪም ቤት የጤና ምርመራ አድርገው ክትትል እያደረጉ የነበረ ቢሆንም በህክምና ቀጠሯቸው ቀን ወደ ሀኪማቸው እንዳይሄዱ የእስር ቤቱ አዛዥ ከልክለዋል:: በዚህም ከፍተኛ ስቃይ ላይ ናቸው:: ወይዘሮ አስቴር ስዩም በጀርባ ህመም እየተሰቃዩ ሲሆን ህመሙን ለመቋቋም የሚያስችል ምኝታም ሆነ ህክምን አላገኙም:: ጨቅላ ልጃቸውን ቤተሰቦቻቸው እያመላለሱላቸው ዕለት በዕለት የሚየያጠቡ መሆኑ ደግሞ ጉዳዩን አሳዛኝም ጭምር አድርጎታል::

በገሃድ ይህ እየተደረገ ባለበት ወህኒ ቤት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀንን እንደማክበር ያለ መንግሥታዊ አላጋጭነት ስለመኖሩ እንጃ:: የአብይ አሕመድ አገዛዝ በአንድ በኩል ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ተቆርቋሪ ሆኖ በመቅረብ በሌላ በኩል ደግሞ የመብቶች ሁሉ ደፍጣጭ በመሆን የቀጠለበትን አደናጋሪ አገዛዝ እንዲያቆም መላው ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያዊነት ጉዳይ የሚገደው የሰው ዘር ሁሉ ሊቃወመው ይገባል:: አደናግሮ የመግዛቱ እንቅስቃሴ የኦሕዴዱ ጓዳቸው አቶ ሽመልስ አብዲሳ ከተናገሩ አደናግሮ ወይም አግባብቶ የመግዛት መርሆ የተጨለፈ ነው::

በመሆኑም ‹ገለልተኛ ነን› የሚሉ የሰብዓዊ መብት ተቋማት ይህንን በማውገዝ እና በማጋለጥ የበኩላቸውን ሓላፊነት ሊወጡ ይገባል:: የግልም ሆኑ የመንግሥት የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ብሎም ህብረታቸው በየእስር ቤቱ እየተሰቃዩ ላሉ የህሊና እና የፖለቲካ እስረኞች መብቶች መጠበቅ በትጋት ሊሠሩ ይገባል:: በየእስር ቤቶች ተገኝተው ተከታታይ ጉብኝቶችን ሊያደርጉ፣ ያዩትን ሐቅም እውነታው ሳይዛነፍ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሁም ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ እንዲያሳውቁ የተቋቋሙበት አላማ ያስገድጋል::

በተመሳሳይ መገናኛ ብዙሃን የገዥውን ፓርቲ የከበሮ ዲልቃ ተከትለው ከሚያሳዩት አስረሽ ምችው ጭፈራቸው ወጥተው ስለ ሰብዓዊ መብቶ መከበር ሊዘግቡ ይገባል:: መንግሥት ተቀናቃኞቹን እስር ቤት አጉሮ የሚያደርስባቸውን በደሎች ሊያጋልጡ ይገባል:: የአራተኛው የመንግሥት አካልነታቸው አንዱ ማሳያም ይህንን በድፍረት ማድረግ መቻላቸው ነው:: የገዥውን ፓርቲ ጥሩምባ ሰምተው የሚጮሁ፤ የመንግሥትን ዜማ ተከትለው የሚያሽበሽቡ ብቻ ከሆኑ ግን በስማቸው ሊያፍሩ ይገባል::

በአጠቃላይ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ በወያኔ/ኢሕአዴግ ሲደረግ እንደነበረው ሁሉ አሁንም ቀጥሏል:: ይህንን ማድረጉ ለወያኔም እንዳልጠቀመው አውቆ የአብይ አሕመድ አገዛዝ ከእኩይ ተግባሩ ሊቆጠብ ይገባል:: ይህ ካልሆነ ግን ሁሉንም ከሚታዘበው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዋጋውን ያገኛል::

**ባልደራስ ጋዜጣ**
መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም.
ተመሰረተ

በየ15 ቀኑ የሚታተም

**አሳታሚ**
ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ
ፓርቲ (ባልደራስ)

**ዋና አዘጋጅ**
ጌጥዬ ያለው
ክፍለ ከተማ፡- ቂርቆስ
ወረዳ፡- 02 የቤት ቁጥር፡- አዲስ
ስልክ፡- +2519 24 51 70 77
ኢ-ሜይል፡- newsgett@gmail.com

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ወግደረስ ጤናው

**አምደኞች**
ገለታው ዘለቀ
ኢንጂነር ጌታነህ ባልቻ

**አርታዒ**
መሶበወርቅ ቅጣው
ነብዩ ውብሸት

**ፀሐፊ፡-** ሕይወት ዳዊት

**የገፆች ቅንብር** ሐብ-ዲዛይን

**ገፀ ድር አስተዳደር** ኢስያስ ፅጉ

# የእነርሱን ጉዳይ ብቻ በየቀኑ የሚከታተል ዕለታዊ ችሎት እንዲሰየም እነእስክንድር ነጋ ጠየቁ

በእስር ላይ የሚገኙት የባልደራስ ከፍተኛ አመራሮች ማለትም እስክንድር ነጋ፣ ስንታየሁ ቸኮል፣ አስቴር ስዩምና አስካለ ደምሌ በ1998 ዓ.ም. በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የክስ መዝገብ እንደተደረገው ጉዳያቸው በየቀኑ እንዲታይ ጠይቀዋል:: ለእነርሱ ጉዳይ ብቻ ራሱን የቻለ ችሎች እንዲቋቋምም አሳስበዋል:: የነፃነት ታጋዮቹ የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲፋጠንላቸውም ጭምር ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት እና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት በደብዳቤ ጥያቄያቸውን አቅርበዋል:: የደብዳቤው ሙሉ ቃል ቀጥሎ ይነበባል፡-



**እነ እስክንድር ነጋ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዘደንት እና ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዘደንት የፃፉት ደብዳቤ**

ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዘደንት
እና
ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዘደንት

**ጉዳዩ፡-** የተፋጠነ ፍትህ ስለመጠየቅ

በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት እነ እስክንድር ነጋ በተከሰስንበት የወንጀል መዝገብ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምክንያቶች አቅርበን፣ ጉዳያችንን የያዘው ችሎት የተፋጠነ ፍትህ እንዲሰጠን መጠየቃችን ይታወሳል፡-

1ኛ. ተከሳሾች በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት አባላት መሆናችንን፣

2ኛ. የታሰርነው በያዝነው ዓመት ይደረጋል ተብሎ እቅድ በተያዘለት ምርጫ ለመሳተፍ በዝግጅት ላይ በነበርንበት ጊዜ መሆኑን፣

3ኛ. የክሱ አላማ፡-

ሀ. ጥፋተኝነታችንን በፍ/ቤት አረጋግጦ ለማስቀጣት አለመሆኑን

ለ. በኮቪድ 19 ሳቢያ ተዘግተው የቆዩት ፍ/ቤቶች ያሉባቸውን የተደራረቡ መዝገቦች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ዋስትና የሚያስከለክል ክስ በመመስረት ጉዳዩ በእንጥልጥል እያለ በምርጫው እንዳንሳተፍ ማድረግ መሆኑን፣

ሐ. በምርጫው እንዳንሳተፍ በፈጠራ ክስ የታሰርን መሆናችንን፣

መ. በተዘዋዋሪም ቢሆን፣ ፍ/ቤት የዚህ ህገ-ወጥ ተግባር ተባባሪ መሆን እንደሌለበት፣

4. ፍ/ቤቱ ከምርጫ ጋር ባሉታዊ መልኩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ላለመነካካት ለመዝገቡ ፈጣን ውሳኔ መስጠት እንዳለበት፣ ይህንንም ለመተግበር የሚከተሉትን የመፍትሄ እርምጃዎች አስፈላጊ እንደሆኑ፣

ሀ. በ1998 ዓ.ም በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል መዝገብ እንደተደረገው፣ ይህን መዝገብ ብቻ የሚመለከት ችሎት እንዲቋቋም፣

ለ. እንደገና፣ በ1998 ዓ.ም በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል መዝገብ እንደተደረገው ጉዳዩ በየእለቱ በተከታታይ እንዲታይ፣

ሐ. በምርጫው የሚሳተፉ እጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት በመዝገቡ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት አሳስበናል::

በዚህም መሠረት፣ ጥቅምት 12 ቀን 2013 ዓ.ም በነበረን ቀጠሮ ምላሽ እናገኛለን ብለን ጠብቀን የነበረ ቢሆንም፣ በዕለቱ ተግባራዊ ምላሽ ሳናገኝ ቀርተናል:: ችሎቱ በሰጠን የቃል ምላሽም፣ ጥያቄያችንን ለበላይ አካል አቅርቦ ምላሽ እንዳልተሰጠው አስረድቶናል::

ስለዚህም፣ አሁን ጥያቄያችንን የበላይ ስለሆናችሁ የህግ ተርጓሚው አካላት እያቀረብን ሲሆን፣ በሀገራችን በቀጣይነት የሚደረገው ምርጫ ፍትሃዊና ሰላማዊ እንዲሆን በዚህ በኩል አስተዋፅኦ እንድታደርጉ በትህትና እንጠይቃለን::

ከሠላምታ ጋር

1ኛ. ተከሳሽ እስክንድር ነጋ
2ኛ. ተከሳሽ ስንታየሁ ቸኮል
3ኛ. ተከሳሽ ቀለብ ስዩም
4ኛ. ተከሳሽ አስካለ ደምሌ

ግልባጭ፡-
ለኢትዮጵያ፡- ምርጫ ቦርድ
ለኢትዮጵያ፡- ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

እነእስክንድር ባለፈው ሕዳር 29 ቀን ፈርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ለፊታችን ታህሳስ 13 ቀን 2013 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ ተቀጥረዋል:: ‹‹ሀሰተኛ የፌስቡክ አድራሻ በመጠቀም የተሳሳተ መረጃ አሰራጭተዋል›› ሲል ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ ላይ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎታል:: በተመሳሳይ የ6ኛ እና የ7ኛ ተከሳሾች ክስ ውድቅ ተደርጓል:: እነኝህን ተከሳሾች ከሳሹ ዐቃቤ ሕግም ሆነ ሌሎች የችሎቱ ተዋንያን በስም፣ በመልክ፣ በምስል ወይም በሌላ ሁኔታ ማወቅ አልቻሉም ነበር:: ስለጠረጠረበት የወንጀል ምንነትም ዐቃቤ ሕግ ማስረዳት አልቻለም:: ስማቸውን መጥቀስ ያልቻላቸውን ተርጣሪዎች ‹‹ከእስር ቤት ያመለጡ ናቸው›› በማለት ዐቃቤ ሕግ መከራከሩ ደግሞ ችሎቱን አወዛጋቢ አድርጎታል:: ክሳቸው የተቋረጠውም ተጨባጭ ማስረጃዎች ማቅረብ ባለመቻሉ ነው:: ከዚህ በፊት ከመጋረጃ ጀርባ ይሰጥ የነበረው የምስክሮች ቃልም በግልፅ ችሎት እንዲሆን ወስኗል::

# ከመንግሥት ያፈነገጡ የመከላከያ አባላት ከፊል የትሕነግ መሪዎችን ጫካ ውስጥ አገቱ

ከፊል የአሸባሪው ትሕነግ/ወያኔ መሪዎች በመዋጋት ላይ እንዳሉ ተጠልፈው በግልፅ ባልታወቀ ጫካ መታገታቸውን ወታደራዊ የመረጃ ምንጮች ለባልደራስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አረጋግጠዋል። አሸባሪዎቹ የታገቱት ቀደም ሲል በእነርሱ ታግተው በቆዩት የሀገር መከላከያ ሰራዊት የሰሜን ዕዝ አባላት ነው። የዕዙ አባላት የበቀል እርምጃ ሊወስዱባቸው ስለመዘጋጀታቸው ምንጮች ጠቁመዋል።

መንግሥት አሸባሪዎቹ ተላልፈው እንዲሰጡት ቢጠይቅም በዚሁ ጉዳይ ብቻ ከመከላከያው ያፈነገጡ የሰሜን ዕዝ አባላት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከታገቱ 3 ቀናት ተቆጥረዋል።

ከትሕነግ ከፍተኛ መሪዎች መካከል ከፊሎችን የአማራ ፋኖ ጠለምት፤ ድማ፤ አምስት ኪሎ ሜትር በሚረዝመው ፍየል ቤት ዋሻ ውስጥ ማርኳቸዋል። ገሚሶቹ ሳይገደሉ እንዳልቀሩም ጦር ግንባር የሚገኙ ምንጮች አረጋግጠዋል። ፋኖ በቁጥጥር ሥር ካዋላቸው በኋላ መከላከያ ቢረከባቸውም ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ወደ አዲስ አበባ ልመጡም። ይሁን እንጂ መንግሥት የመያዛቸውን ዜና ይፋ አላደረገም።

በአሸባሪው ወያኔ እና አማራ ፋኖ ብሎም የአማራ ልዩ ሃይል በተደረገው ጦርነት ጠገዴ፣ ማክሰኞ ገበያ፣ ሽመልጌ፣ ጠለምት፣ ጥቁር ውሃ፣ ወፍ አርግፍ፣ ሀገረ ማርያም እና ካድራ ወንዝን ጨምሮ የወልቃይትና ጠለምት አካባቢዎች ወደ ነበሩበት የጎንደር/አማራ ግዛትነት ተመልሰዋልል። ካድራ ወንዝን (ማይካድራ) በአንዳንድ ከተሞችም የአማራ ወጣቶች ማሕበር ተመስርቷል።

# ኦነግ በወለጋ ወደ 60 አማራዎችን ገደለ የ3ቱን ምላስ ቆርጧል

በኦሮሚያ ‹ክልል› ወለጋ፤ ነቀምት ጊዶ ድሬ ቀበሌ ባለፈው ታህሳስ 1 ቀን 2013 ዓ.ም. በትጥቅ ትግል ላይ የተሳማራው ኦነግ ወደ ስልሳ የሚጠጉ አማራዎችን መግደሉን ከግድያ የተረፉ ምንጮች ተናገሩ። ግድያው ሲፈፀም በቦታው ከነበሩ አማራዎች መካከል ከፊሎቹ ምላሳቸው ተቆርጧል። ወደ 3 መቶ የሚጠጉ አማራዎች ደግሞ ግድያው ከተፈፀመበት ዕለት ጀምሮ የደረሱበት አልታወቀል። ሸሽተው ስለ ማምለጣቸው ወይም በገዳዮች ስለመታገታቸው ምንጮች ርግጠኛ መሆን አልቻሉም። ሟቾች ጥቃት ሊሰነዘርባቸው እንደሆነ አስቀድመው ለመንግሥት ቢያሳውቁም የደረሰላቸው አካል የለም።

በተመሳሳይ በቀድሞዋ የጎጃም ግዛት መተከል፤ ዳንጉር ወረዳ ቆታ ቀበሌ ታህሳስ 2 ቀን 2013 ዓ.ም. የጉምዝ ታጣቂዎች አንድ የአማራ ተወላጅን በ11 ጥይት ደብድበው ገድለውታል። ታጣቂዎቹ ሰውየው ከተገደለ በኋላም አስክሬኑን ደጋግመው በጥይት ተኩስ መደብደባቸውን የዓይን እማኞች ገልፀዋል።

ይህንን የተረዱት የአማራ ፋኖዎች ወደ ቤንሻንጉልና ኦሮሚያ ‹ክልሎች› ለጦርነት ለመዝመት ለአማራ ‹ክልል› መንግሥት ጥያቄ አቅርበዋል። ይሁን እንጂ መተከል በከፊል የገቡ ሲሆን ወደ ኦሮሚያ እንዳይገቡ ተከልክለዋል።

# አባ ገዳዎች በደራ ቡድን ለመመሥረት እንቅስቃሴ ጀመሩ

በአማራ፤ ሸዋ፤ ደራ ወረዳ ውስጥ የኦሮሞ አባ ገዳዎች ስብስብ ለመመሥት እንቅስቃሴ መጀመሩን የደራ አማራ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴ አስታወቀ። ‹‹አንዳንድ ሆድ አደር የኦሮሙማን ተልዕኮ አንግበው የሚንቀሳቀሱ በእድሜ የገፉ ‹የሀገር ሽማግሌ ነን› ባዮች በገንዘብ ተደልለው ማንነታቸውን በመሸጥ አባ ገዳን በአማራዎች ላይ ለማቋቋም እንቅስቃሴ ጀምረዋል።›› ብሏል ኮሚቴው። ይሁን እንጂ የገዳ እንቅስቃሴ ከባእድ አምልኮ ጋር የተቆራኘ መሆኑን በመግለፅ ሕዝበ ክርስቲያኑም ሆነ ሕዝበ ሙስሊሙ እንደማይቀበለው ጠቁሟል። የደራ ሕዝብ ባህሉም ሆነ ሌላው መስተጋብሩ ከመርሐቤቴ ዘመድ አዝማዱ ጋር ፈፅሞ ተመሳሳይ መሆኑን የገለፁት የደራ አማራ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴ የሥራ ሓላፊ ከአባ ገዳ እንቅስቃሴ ጋር የሚቀራረብ ታሪክ እንደሌለው አስረድተዋል።

የደራ ሕዝብ የአማራ ብሔር ተወላጅ ሲሆን ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በወያኔ/ኢሕአዴግ ወደ ኦሮሚያ ‹ክልል› በኃይል ተካልሎ ይገኛል። በገዳ እንቅስቃሴ በየስምንት ዓመቱ ሥልጣን ከአንደኛው ገዥ ወደ ሌላኛው በሚሸጋገርበት ወቅት በሌሎች ሕዝቦች ላይ የሚደረግ ወረራ አለ። በዚህ ሂደትም ከ28 በላይ ነባር የኢትዮጵያ ነገዶች መጥፋታቸውን ታሪክ ያስረዳል። በእንቅስቃሴው ውስጥ ገዥዎች የሚመሰገኑት በሞጋሳ ወይም ገበሮ አስተሳሰብ የሌላውን ማንነት እያጠፉ ኦሮሚዊነትን ባስፋፉበት መጠን ልክ ነው።

# ውስጠ ወይራው ያለመለወጥ ‘ለውጥ’

በቃሉ ሰውመሆን (የሕግ ባለሙያ)

## አቢቹ ሰብሮ የወጣው ወያኔ የጣለውን እቁላል ነው፤

በጥቅሉ ከ 1960 ዓ.ም ወዲህ እስካለንበት በተከሰተው እንዘጭ እቦጭ ውስጥ ኢትዮጵዊነትን ለከፍተኛ ኪሳራ የዳረገ እራስ በል እና እራስበሉን አስቀጣይ የሆነ ሽግግራዊ ክሽፈት አጋጥሞናል፤ አንደኛው የክሽፈት አንጓ የንጉሳዊ ስርአቱን አንጻባራቂ ውርሶች አዘምኖ ማሸጋገር ሲገባ ለአውዳሚ አቢዮት መዳረጋችን ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የኢሕአዴግን አራሙቻ ስርአት የሚነቅል አብዮታዊ የስርአት ለውጥ ማዋለድ ሲገባን ጠጋግነን ማስቀጠላችን ነው:: ቅኝ እንደተገዛ ህዝብ ከኢትዮጵዊነት ጥነተ ውርስ እና ሀገር በቀል የእውቀት መሰረት ላይ ተነቅለን ተቅበዝባዥ እንድንሆን የዳረገን የፖለቲካ ታሪካችን አንዱ ዝንፈት ይህ ይመስለኛል:: አብዮት ለማይገባው አብዮት፤ ለሚገባው ደግሞ የአስቀጣይነት ሥራ ነው የተሠራው:: በተለይ የያኔው ትውልድ የኢትዮጵያዊ ብሄርተኛ መልካም እሴቶቻችን እና ተቋማትን ተከላክሎ እና ዘመኑን እንዲዋጅ አድርጎ ማስቀጠል ሲገባው፤ ከጭቃ እሾህ ዘውገኞች ጋር አብሮ ተሰልፎ የኢትዮጵያዊነትን ጎን መሸንቆሩ ከታሪክ ተዋቅሽነት አያድነውም:: ከመሰረታችን ተነቅለን ስናበቃ ነቃዩን አስተሳሰብ ደግሞ ለማስቀጠል ከመዋተት ያለፈ ምን እራስበልነት አለ:: መንቀል እና ማስቀጠል ያለብንን ውርሰ መሰረት ካላወቅን ዘላቂ ስርዓት ማንበር ተስኖን ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉት ለእዘጭ እቦጭ ተዳርገናል:: የስርዓት ለውጥ የሂደትም የግብም ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ጅምሩን እና ሂደቱን ካለጎምነው ውጤቱ እዘጭ እቦጭ ይሆንና በለውጥ ሽፋን ተረኛ ጨቋኝ የማንበር አዙሪት ውስጥ መዳከርን ያስከትላል:: የሀገራችን ፖለቲካዊ ስነ ልቦና ትልቁ ጠባሳ ይህ ስለመሆኑ የሀሳቡ ተጋሪ ነኝ:: ለአምባገነኖች በአድር ባይነት አድፍጦ መገዛት፣ ገንፍሎ መንቀል እና መልሶ አምባገነን ማንበር፤ ለዚህ አዙሪት ዋናው መንስኤው ዘለቄታዊ ስርዓት ከማዋለድ በፊት የእርካብና መንበርን መሰላል የመጨበጥ ግለኝነት አስተሳሰብ ቀድሞ የመጋረጡ አባዜ ይመስለኛል::

ህዝባዊ ስርዓትን ጻነሰን ስናበቃ አገዛዝን እያዋለድን ቀጥለናል:: ከለውጥ ተብዬው ወዲህም እየሆነ ያለው ይሄው ነው:: በየትም በኩል ለውጥ ይከሰት መሰረታዊ የስርዓት ንቅለ-ተከላ ማስፈን የመጨረሻ ግብ መሆን ነበረበት:: “በለውጡ” ዋዜማ ህዝባዊ ትግሉ ፍሬ ሊያፈራ የሚችልበት መንታ የቢሆን ትንታኔዎች እንደ ጉም እየተነኑ ነው፤ በአንድ በኩል ህዝባዊ ትግሉ የመንግሥትን መዋቅር ከውጭ ወደ ውስጥ የሚያጸዳ የለውጥ ምዕራፍ ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮ አንድም ውርሰ-ስንጥቁ አገርሽቶ የርስበርስ ሽኩቻ ሊከሰት ይችል ነበር፤ አሊያም የደፈረሰው ጠርቶ ክሱት ስር ነቀል የስርዓት ለውጥ የማዋለድ ዕድል ይፈጠር ነበር:: ሁለተኛ የህዝቡን የለውጥ ፍላጎት ከሚጋራ የውስጥ ሀይል ጋር የተቀናጀ እና ከውስጥ ወደ ውጭ የሚፈነዳ አዝጋሚ ስር ነቀል የሽግግር ሂደት መጠንሰስ ነበር:: ይህም ለክሱት ሽግግር የሚከፈለውን ዋጋ ሊቀንሰው ይችላል:: ለለውጥ ተብዬውም ድጋፍ የተቸረው ከዚህ አኳያ ነበር:: የሆነው ግን ህዝባዊ ትግሉ የመንግስትን መዋቅር አጽድቶ ወደ ስርዓታዊ ሽግግር ከማምራቱ በፊት የህዝቡን መሰረታዊ የለውጥ መሻት የሚያዋልድ መስሎ የሚያጨነግፍ አስመሳይ የውስጥ ሀይል ነው የተከሰተው:: በመሆኑም ሀገራዊ መሻትን በቡድናዊ መሻት እና ተረኛ ጨቋኝ ለሚለውጥ ቁልቁለት ተዳርገናል:: የአስቀጣዩ ዳግማዊ ኢሕአዴግ ውስጠ ወይራ አላማው ከውርሰ-መሰረቱ በአውዳሚ አብዮት የተዳፈነውን የኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ከፖለቲካዊ ውክልና እንደተነቀለ አንሳፎ ማስቀረት ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ በአብዮታዊ ለውጥ መነቀል የነበረበት ኢሕአዴጋዊ ውርሰ ጥፋት በለውጥ ሽፋን አለባብሶ ማስቀጠልን ያለመ ነው:: የለውጥ ተብዬው መዘውር መንትዮሻዊ ፍላጻ ያለው ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን አዳፍኖ ማቆየት እና የዘውግ አረሙን ደግሞ አስቀጥሎ ምርቱን መሰበሰብ ነው::

በመሆኑም በተለይ ከኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው አኳያ በለውጥ መሻቱ እና በለውጥ ሽፋን እየተሰራ ባለው ተግባር መካከል መሰረታዊ መዛነፍ፣ ተቃርኖ እና መተላለፍ ተፈጥሯል:: በኢሕአዴግ ፍጻሜ ላይ የለውጥ መሻቱ እውን መሆን ሲገባው በአንጻሩ በለወጡ ኪሳራ ኢሕአዴግን ከነጥንተ ርእዮቱ የማዳን ሥራ እየተሠራ ነው:: “የለውጥ ሀይል” ተብዬው መሰረታዊ ጭንቀት ስር ነቀል ለውጥ ከመጣ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት አብዮታዊ ውድመት (በ1960) ከማስተናገዱ በፊት ወደነበረ ልዕልናው ያንሰራራል የሚል ነው:: ሁኔታው የሚከፋው ደግሞ ኢሕአዴግ ከተፈጥሯዊ እና ከሚገባው የፖለቲካ ሞቱ እንዲያንሰራራ እየተደረገ ያለው በአዲስ ርእዮት፣ ሕገ መንግሥታዊ እና መዋቅራዊ ለውጥ ሳይሆን የነበረውን ቡቱቶ ደርቶ በማስቀጠል ነው:: እየሆነ ያለው ድራፍት እንዳይጠጣ በሀኪም ለተከለከለ ሰው ቢራ እንደማጠጣት ያክል ነው:: ታማሚው ያንኑ እየተጋተ አዲስ መድሃኒት እንደተገኘለት ያክል ይቦርቃል:: በለውጥ ሽፋን ለውጥን የመከላከል ስልት፤ ወደፊት እያዩ ወደኋላ የመራመድ የአስመሳይነት፣ የአበያነት እና የልግመኛነት ቁልቁለት ውስጥ ነን:: ለውጡን እናግዝ እያለ ትውልድን የሚያደናግረው የፖለቲካ አደንጓሪ በኢሕአዴግ እና በዳግማዊ ኢሕአዴግ(ብልጽግና) መካከል መሰረታዊ የርዕዮት ልዩነት ስለመኖሩ ምን ማሳያ አለው? በአመዛኙ በሂደት ይለወጣል የሚል መከራከሪያ ሲያቀርቡ ይደመጣል:: ቀድሞውንም ጥያቄው ያለው ጥንስሱ ላይ ነው እንጂ በአንድ ጀምበር ሁሉ ይከሰት የሚል አይደለም:: ዳግማዊ ኢሕአዴግ ርዕዮቱን ሳይቀይር ዘዋሪውን ብቻ ቀይሮ የተረኝነት ሀዲድ ላይ አሳፍሮን ሳለ በሂደት የሚጠበቀው ለውጥ ከተረኛ አስቀጣይነት ሊዘል ይችላል ወይ? ፖለቲካችን የሚያስፈልገው እንቁላሉን ሰብሮ የሚወጣ የውረሰ ጥፋት አስቀጣይ ሳይሆን እንቁላሉን እራሱን የሚቀይር ስርዓታዊ ለውጥ ነው:: አቢቹ ሰብሮ የወጣው ወያኔ የጣለውን እቁላል መሆኑን አንዘንጋ:: ለዚህም ነው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛው በራሱ ጥንተ ውርስ እና ማህበራዊ መሰረት ላይ በተበባበረ ክንድ ለትግል መነሳት አለበት የምንለው:: የሆነው ሆኖ በለውጥ ሽፋን ለውጥን የመከላከል ቁልቁለቱ አያሌ ርዕዮት-አለማዊ፣ ተቋማዊ፣ ህገ መንግስታዊ እና ስርዓታዊ መገለጫዎች አሉት:: እነሆ በቅጭቡ፤

ሀ/ የአዳፍኔነት እና አስቀጣይነት መንታ ስለት፤

የሚዳፈነው ማን ነው? የሚቀጠለውስ? የሀገራችን ፖለቲካ በተውሶ ጥብቆ መቀንበብ ከጀመረበት የተማሪዎች አብዮት ጀምሮ በተለይም ከወያኔ መከሰት ወዲህ በመሰረታዊነት በሁለት የፖለቲካ አሰላለፍ ተቃርኖ ተሰቅዟል:: የተቃርኖው ስንጥቁ በዋናነት ከላይ ከተገለጸው የሽግግር ክሽፈት አንጻ፣ ከታሪክ አረዳድ እና የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ ተቃርኖ ይመነጫል:: ክሱት ብያኔውም የመደብ እና የዘውግ ጭቆና ትርክት በሚለው ይሸከፋል:: በጥቅሉ የስንጥቁ አንድ መከሰቻ ከኢትዮጵዊ ውርሰ-እሴት የሚቀዳው ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት/civil nationalism ሲሆን ሌላኛው የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት ላይ የተጠነሰሰው የዘውግ ብሄርተኛው/ethnic nationalism ነው:: ወያኔ የተቀዳችበት ኸረት በቅኝ ገዢዎች ሀገር አፍራሽ ሴራ ተጣብቶ፣ በራስ በሉ ሌኒኒስታዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ታጅሎ በሻቢያ አውቆ አጥፊ ትርክት አጎንቁሎ አንቀጽ 39 ላይ የተቋተ የደም እዳ ነው:: በአመዛኙ የዘውግ ጭቆና ትርክት መሰረቱ የእውነታ ጥመት/Distortion ነው፤ በነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ እውነትን ሳይሆን የሚበጀውን ሀሰት ፈጥሮ፣ ለነበረው እውነት አዲስ ትርጉም ሰጥቶ ለፖለቲካ ፍጆታ የማብቃት ጥመት ነው:: ጥመት ደግሞ ከዜሮ ጀምሮ፣ በራሱ ኸረት ቀልብሶ የሚፈስ እና ሁሉን በራስ የመለወጥ ውርሰ ጥፋት ነው፤ የሻቢያ፣ የወያኔ እና የኦነጋውያን ርእዮት ውርሰ መሰረቱ፣ የፍሰት አቅታጫው እና መዳረሻው ስልቻ ቀልቀሎ ቀልቀሎ ስልቻ እነደሚባለው ከዚሁ የሚቀዳ ነው::

ሀገሪቱ የቆመችበትን መሰረታዊ የህላዌ ምሰሶዎችን ለግዜያዊ የፖለቲካ ትሩፋት መሰዋት፣ ማጠልሸት፣ እንደ አዲስ መበየን፣ ከዜሮ መጀመር፣ በቅልብስ እሳቤ እና ቁልም አረዳድ የታጀለ ነው፤ የቁልቁለቱ መዳረሻ ራስ ጠልነት ነው:: የ“ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች” ምናባዊ ምስል ክሰታ፣ የተጨቋኝነት እና ቅኝ ተገዥነት ተረት፣ የአማራ ጨቋኝነት የጋራ ጠላት ምስል ክሰታ፣ እራስን በራስ... እስከመገንጠል፣ ወዘተ እውነታን እንደሚበጅ አጣሞ ለነበረው አዲስ ትርጉም መስጠት የፖለቲካ ትርፍ ማሳለጫ እና የትግል መሳሪያዎች ናቸው:: በሌኒኒስታዊ የዘውግ ጨቋኝ-ተጨቋኝ የፖለቲካ ትርክት ውስጥ ሁሉም ነገር የትግል መሳሪያ ነው:: እግዚያብሄርን ከመካድ ይነሳል፤ ታሪክ፣ ሀገር፣ ተቋማት(የሀይማኖትም ሆነ ማህበራዊ) ሰው፤ መሬት ሁሉ የፖለቲካ ትጥቅ ነው:: በትግሉ ውስጥ የሚከሰቱ ስብእናዎችም እራሳቸውን የጥቅሉ አለም ወይም የሀገር አንድ አካል አድርገው አይረዱም:: ይልቁኑ ሁሉም ነገር ለነሱ ሲል የሚኖር የሚመስላቸው ግላውያን/narcist ሲሆኑ እራሳቸውን ብቻ እንደግብ ያያሉ:: በዚህ ቁልቁለት ወያኔ ስንጥቁን አስምሮ ሲያበቃ ከስንጥቁ አንዱን(የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክትን) በዋና መሳሪያነት ተጠቅሞ የሀገሪቱን ሁለንተና እንደ ነቀዝ በልቶ ለአስቀጣዩ አስረክቦታል:: አብላጫ ማህበራዊ ቅቡልነት እያለው ከፖለቲካ ውክልና ተገፍትሮ በተንሳፋፊነት ይልበላውን እያከከ የቀጠለው ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው ነው::

ከዚህ አኳያ “የለውጥ ሀይል” ነኝ ባዩ አቢቹ(ኦነጋውያን) ተልእኮ እንዴት ይመዘናል? ላለፉት ሁለት አመታት በነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ፣ በትርክት እና በተግባር እንደታየው እነ አቢቹ የጨቋኝ- ተጨቋኝ ትርክት ወራሾች እና አስቀጣዮች ለመሆናቸው በቂ ማሳያ አለ:: ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው እዚህ ላይ ብዥታ ውስጥ ገብቶ እራሱን ባያታልል መልካም ነው:: ማሳያውን ሁሉ መተንተን ለቀባሪው እንደ ማርዳት ነው:: የመደመር መጽሀፍ እስኳል መልክቱ የጨቋኝ ተጨቋኝ ርእዮት አስቀጣይነት ነው፣ የሽመልስ አብዲሳ ሰበርናቸው ትርክት እና አማራን እያጠፋነው ነው ድብቅ ንግግር፣ የአቢቹ የአስከሬን ዘር ቆጠራ እና ለአንድ ብሄር ብለን ህገመንግስት አናሻስልም ንግግር፣ ወዘተ ውስጠ ወይራ መልእክቱ የተዳፈነውን ኢትዮጵዊ ብሄርተኝነት አዳፍኖ ማቆየት እና መራሹን የዘውግ ፖለቲካ አረም ደግሞ አስቀጥሎ ምርቱን መሰበሰብ ነው:: የአዙሪቱን አንድምታ ከለውጥ ተብዬው አኳያ በዚህ መልክ ልቀንብበው፤

1ኛ እነ አቢቹ የፖለቲካ ውርሰ ስንጥቁን ለፖለቲካ ሚዛን ማስጠበቂያነት መጠቀማቸው አስቀጣይነት አንድ ማሳያ ነው፤ በስንትቁ ተቃርኖ የተሰቀዙትን አሰላለፎች እንደ ጽንፈኛ በመሳል እራሳቸውን በመሀል ሰፋሪ እና በለዘብተኛነት አቅርበው የቅቡልነት ማሳለጫ ቢያደርጉትም እራሳቸው በስንጥቁ አንድጫፍ የሚሰለፉ ናቸው:: 2ተኛ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ቀና ለማለት ሲሞክር በጽንፈኝነት ፈርጆ የማደከም ልምምድ ያላቸው መሆኑ ሌላው የአዳፍኔነት ማሳያ ነው:: በመሰረቱ ልብ ማለት የሚገባው ኢትዮጵዊ ብሄርተኝነት የፖለቲካ ተቃርኖው ጥቅል አሰላለፍ ማሳያ እንጂ በራሱ ጽንፍ አይደለም:: ምሰሶው እንዴት ጽንፍ ይሆናል? አሜሪካዊነት ለአሜሪካውያን ጽንፍ ይሆናል ወይ? ከዚህ አኳያ እየተሰራ ያለው ሴራ ሆን ብሎ ሀሳዊ መንትዮሽ/false dichotomy እና ሀሳዊ ንጽጽር/false equivalence በማስረጽ ምሰሶውን(ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን) ከመሀል የመገርሰስ፣ ገርስሰው ሲያበቁ መሀል መንገድ ላይ እንገናኝ በሚል ፈሊጥ ጭብጦውን ይዞ ወደምሰሶው የመንኳተት፣ ብሎም መሀሉን ለብቻ የመጠቅለል እና የመሰልቀጥ አደገኛ አካሄድ ይስተዋልበታል:: ሰዋዊው እስክንድር እና ዘውገኛው ጀዋር በጽንፍና ጽንፍ የሚፈረጁ ናቸው ወይ? የሰማይ መሳላል የሆነችው ሰንድቅ አላማችን እና የድርጅት አርማው የኦነግ ባድራ በጽንፍና ጽንፍ የሚፈረጁ ናቸው ወይ? OMN እና የድሮው ESAT ወይም ያሁኑ መረጃ ቲቪ በጽንፍና ጽንፍ የሚፈረጁ ናቸው ወይ? እውን የአማራ ራስን የመከላከል ተፈጥሯዊ ብሄርተኝነት እና እራስ ጠሉ የዘውግ ብሄርተኝነት የሚነጻጸ ናቸውን? ይህ ሁሉ የሀሳዊ መንትዮሽ/false dichotomy እና ሀሳዊ ንጽጽር/false equivalence ሰሊጡን ከኑጉ ጋር ቀላቅሎ የመውቀት የፖለቲካ ታክቲክ ማሳለጫ:: አሁን አሁንማ እስራት፣ ግድያን እና የአስከሬን ቆጠራን በራሱ በዚሁ መነጽር በብሄር ተዋጽኦ እና ከሁለቱም ጽንፍ የማዳረስ አሰራር እየተለመደ ነው:: ሁኔታው ቅኝ ብንገዛ ኖሮ ይሰራብን ከነበረው ባልተናነሰ የሀገራችንን እና ህብራዊ ማንነታችንን መሰረታዊ እሴቶች የማሳጣት ብሎም ለብቻ የመጠቅለል አደገኛ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ነው::

3ኛ በጓያ አውድማ ላይ ጤፍ መውቃት ሌላው የአዳፍኔነት እና አስቀጣይነት ማሳያ ነው፤ እነአቢቹ(ኦነጋውያን) በትርክት ደረጃ የኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ማቀንቀናቸው ከፖለቲካ ስልትነታ የማያልፍ፣ ግን ደግሞ ውስጠ ወይራ አንድምታ ያለው ነው፤ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት አብላጫ ማህበረሰባዊ ቅቡልነት ቢኖረውም ህገመንግስታዊ እና መዋቅራዊ መሰረት እንዳይቆናጠጥ በወያኔ እና በመሰሎቹ አውዳሚ ስራ ተሰርቶበትል:: ይህን ከማስቀጠል አኳያ በትርክት ደረጃ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን ማዥጎድጎድ የፖለቲካ ማህበራዊ መሰረቱን በማሳከር በጋራ እንዳይቆም ከማድረግ ባለፈ በፖለቲካ መዋቅር ደረጃ ጠብ የሚል ውጤት እንዳማያስከትል እነአቢቹ ያውቁትል:: ምክንያቱም ስንኩል ማህበራዊ መሰረት ኖሮት ሳለ ህገመንግስታዊ እና መዋቅራዊ መሰረት ተቆናጦ ያለው በተጨባች የዘውግ ጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክ በመሆኑ ነው:: መሰረት የያዘውን የዘውግ ፖለቲካ ለማስቀጠል አንዱ ስልት መሆን ያለበት ደግሞ ኢትዮጵዊ ብሄርተኛው እውነተኛ እና መሰረታዊ ሽግግር የሚያስከትል ለውጥ እንዳያዋልድ በመከላከል ነው:: ይኸውም ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛውን በትርክት ሸንግሎ ወደሰገባው በመመለስ ማዳፈን ሲቻል ነው:: በለውጥ ሽፋን ለውጥን የመከላከል አዳፍኔነት እና እስቀጣይነት ይሉሀል እንዲህ ነው:: በተለይ የአቢቹን ፖለቲካዊ ትርክቶች መአከላዊ መልክት ለመረዳት አንዱ ዘዴ ትርክቱን ገልብጦ ማንበብ ጠቃሚ ይመስለኛል:: እያሞገሰ ይቀብርሀል፣ የልብህን እየተናገረልህ በተግባር ያልነገረህን ሴራ ያጎናጽፍሀል:: የኦነጋውያን ዋና አላማ የተካደውን ኢትዮጵዊ ብሄርተኝነት አዳፍኖ ማቆየት እና መራሹን የዘውግ ፖለቲካ አረም ደግሞ አስቀጥሎ ምርቱን ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ በለውጥ ካባ ለውጥን በዘላቂነት መከላከል ነው:: ቀድሞውንም ለመቀልበስ የሚበቃ የለውጥ ፍላጎት እና ጅምር ስላልነበረ ባለንበት ሁኔታ የውድቀት አዙሪት ቀጠለ ነው እንጂ ለውጥ ተቀለበሰ ማለት አይቻልም::

*ለ/ የውርስ እዳ ደብዳቤውን ማን ይቅደደው?*
*(ክፍል ሁለት ይቀጥላል)*



# የደም ፖለቲካው ማዕከል፤- ወልቃይት



ውቤ ደነቀው መኮንን

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ በሀገራችን ሰሜናዊ ምዕራብ ክፍል በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራና ስሜን አውራጃዎች የሚገኙት አራት ወረዳዎች ጉዳይ ከእናት ክፍለ ሀገራቸው ከጎንደር ተገንጥለው በትህነግ/ኢህአዴግ የመስፋፋት አላማና አልጠግብባይነት ወደ ትግራይ መካለላቸው ነው::

እነዚህም ፡- 1ኛ/ ወልቃይት

2ኛ/ ጠገዴ

3ኛ/ ሰቲት ሁመራ የሚባሉት ወረዳዎች ከወገራ አወራጃ

4ኛ/ ከሰሜን አውራጃ ደግሞ ጠለምት የተባለው ወረዳ ከፊል የዋልድባ ገዳምን ጨምሮ በአጠቃላይ አራት ወረዳዎችን ያካተተ የመሬት ወረራ በዘረኛው ትህነግ ከተፈፀመ ከ32 ዓመታት በላይ ተቆምረዋል::

ትህነግ ባንዳውን ኢህዴንን በአምሳሉ ቀርጾ አሰልጥኖና እስታጥቆ የህወሃት የአማርኛ ክፍል /Amharic Department/ ከከፈተበትና በ1980 እ.ኢ.አ ራሱን ኢህአዴግ ብሎ ከሰየመበት ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ የህወሃት ታጋዮች የነበሩት አቶ አብርሃም ያየህና አቶ ገ/መድህን አርአያ በግልፅ ከጎንደር ወልቃይትን፣ ጠገዴን፣ስቲት ሁመራንና ጠለምትን ከወሎ ክፍለ ሀገረ ራያና አዘቦን፣ አላማጣን፣ ዋጃ ጨርጨርንና ኮረምን አጠቃሎ ከትግራይ ጋር በማጣመር የታላቋ ትግራይ የቅዠት ካርታ እንደሰራ ነግረውናል::

ይህንንም ቡድን የኢትዮጵያ ህዝብ በጥንካሬና በቆራጥነት ካልተከላከለውና ካልደመሰሰው በስተቀር ወደፊት ለኢትዮጵያና ለህዝቧ በአጠቃላይ ለአፍሪቃ ቀንድ ጭምር አደገኛ ድርጅት እንደሚሆን በወቅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ በሁሉም መደበኛ የመገናኛ ብዙሀን በግልፅ ያሳሳቡና ያስጠነቀቁ ቢሆንም አምኖ የሚቀበላቸው መንግስትም ሆነ ህዝብ አለማግኘታቸውን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በሀዘን ያስታሳል::

በመሠረቱ አቶ አብርሃምና አቶ ገ/መድኅን ከህወሃት አፈንግጣው በመውጣት ሊወሰዱ የታሰቡትን ቦታዎች ጠቅሰው ይንገሩን እንጂ ይህ ጠባብና አፍራሽ ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ገና ከምስረታው ጀምሮ ለራሱ ከሰጣቸው ስያሜዎች ማለትም፡-

ማገብት/ማህበር ገሥገሥቲ ብሄረ ትግራይ

ተሀህት/ ተጋደልቲ ሀርነት ህዝቢ ትግራይ

ትህነግ/ የትግራይ ህዝብ ነፃነት ግንባር

ሕወሃት/ሕዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ

በመነሳት ስንገመግመው በሙሉ ዘረኝነቱን፣ ተገንጣይነቱንና ወደፊት ትግራይን ከኢትዮጵ ገንጥሎ የታላቋ ትግራይ ሪፐብሊክን ለመመስረት

በስታሊናዊና በአልባያን ኮሚኒዮዝም የተቃኘ አስተዳደር መስርቶ ለሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሰላም ነቀርሳነቱን በግልፅ ሲያሳይ የነበረ የሰይጣን ቁራቾች ስብስብ መሆኑ በብዙ መረጃዎችና ማስረጃዎች የተረጋገጠ እውነት ነው።

ከላይ የጠቀስናቸውን የሰሜን ምዕራብና የሰሜን ጎንደር አራት ወረዳዎችን የመጠቅለል አባዜውንና ወሳኔውን እነ አቶ አብርሃም ያየህ ካረዱን ከጥቂት ዓመታት በኋላ ትህነግ በለሰቀንቶት ኢህአዴግ በሚል ጭምብል ውስጥ ታጅሎ በፊት የተጠቀሱትን ወልቃይትን፣ ጠገዴን፣ ጠለምትንና ሁመራን እንዲሁም ከወሎ ክፍለ ሀገር ላይ የሰሜን ወሎን ለም መሬቶች እና ከአፋር የተወሰደ ክፍል የትግራይ ክልል (በወቅቱ የክልል 1 አካላት ናቸው ብሎ የአዋጁን በጀሮ እንዲሉ በፊት የሰማነውን የእነ አቶ አብርሃም ያየህን መረጃ እውነትነት በግልፅና በትዕቢት አረጋግጠናል።

ይህ ጽንፈኛና አራጅ ቡድን ሀገራችንን ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ከተቆጣጠረበት ከ1983 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) ጀምሮ በወልቃይት ጠገዴ፣ በጠለምትና በሰቲት ሁመራ ነዋሪና ባለርስት ህዝብ ላይ ያደርስ የነበረውን ሰቆቃ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም።

**ከብዙ በጥቂቱ ግን እንደሚከተለው ሊቃኝ ይችላል፡-**

1. ሰው በላው ትህነግ/ኢህአዴግ የተጠቀሱት (ከአማራው አስተዳደር አካባቢ የተቆረሱት መሬት ባለቤቶች፣ ባለርስቶች ታሪክ አዋቂዎች የሀገር ሽማግሌዎችና ነገሩ የከነካቸው የይገባኛል ጥያቄ በሚጠይቁ (ሲጠይቁ የነበሩ ከ3,000 (ሦስት ሺህ በላይ ተወላጆችን በፊት ወደ መቀሌ በኋላም በዶ ስድስት (06) ተብሎ በሚጠራው የትህነግ የማሰቃያና የማረጃ እስር ቤት ተወስደው እስከዛሬ ድረስ ምን ይሁኑ ምን ሳይታወቅ ቀልጠው የቀሩ ዜጎችን ቤታቸውና ቤተሰቦቻቸው ይቁጠሯቸው።
2. ለወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምትና ሰቲት ሁመራ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ትህነግ ለአማራው ህዝብ በሙሉ ባለው ሥር የሰደደ ቂምና ጥላቻ (የበታችነት ስሜት በወለደው ጭፍን ጥላቻ) ምክንያት የአማራ እናቶች፣ እህቶችና የ12 ዓመት ሴት ህፃናት ሳይቀሩ እንዲመክኑና የአማራ ዘር እንዳይቀጥል (እንዲቀንስ) በአሁን ጊዜ የዓለም ጤና ድርጅት ዳይሬክተር (W.H.O) ሆኖ በሚሰራው በዶክተር ቴዎድሮስ አድኃኖም የስልጣን ዘመንና (የጤና ሚኒስትር) መሪ ተዋናይነት የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈፀመበት ህዝብ አካል ነው።
3. በደርግና በትህነግ ሰራዊት መካከል ይካሄድ በነበረው በቅድመ 83ቱ ዓመተ ምህረት ጦርነት አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን በተለይም ታዋቂውን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ገዳምና እየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ እንደ ሰው በሚመላለስበት ጊዜ በኢትዮጵያ ከእናቱ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ከቅዱስ ዮሴፍ ጋር በሊቀ መላዕኩ ቅዱስ ኢራኤል መሪነት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከጎበኛቸውና ባርኮና ቀድሶ ከገደማቸው ገዳማት አንዱና የመጀመሪያው እንደሆነ በሚታመነው ዋልድባ አብርንታት (አብረን ከአንተ) ገዳም ላይ የፈፀሙትና እየፈፀሙ ያሉት ገዳሙን በልማት ስም የማፍረስ ፀረ ተዋህዶ ክርስትና ሴራ በሌላው የሀገራችን ክፍል ከሚደረገው የበለጠና የተለየ ፀረ ተዋህዶ ተግባራት ግንባር ቀደምትነትን የሚይዘው ታላቁ ገዳም የወልቃይትና የጠለምት ወረዳዎች አካል መሆኑ ልዩ የሚያደርገው ጉዳይ ነው።
4. ባለፉት 32 ዓመታት ወያኔ/ትህነግ / ኢህአዴግ አካባቢውን ከተቆጣጠረበት ወቅት ጀምሮ አፍኖ ከሰወራቸው ከ3000 (ሦስት ሺህ) በላይ የአካባቢው ተቆርቋሪ ተወላጆች በተጨማሪ የነበረው ዘረኛና እብሪተኛ ወያኔ አስተዳደር አላስኖር ያላቸው ወጣቶችና አዛውንት አካባቢውን እየለቀቁ ወደ አጎራባች ወረዳዎችና ወደ ጎንደር ከተማ የገቡ ሲሆን በእስር ይማቀቁ የነበሩትንና በግፍ የተገደሉትን አሁንም ቤታቸውን ይቁጠራቸው እንጂ ይኼን ያህል ተብሎ ሊገለጽ አይችልም።
5. ከላይ የተገለፀው በወልቃይት፣ጠገዴ፣ ጠለምትና ሁመራ ለበርካታ ዓመታት የፈፀመው ግፍና ሰቆቃ አልበቃ ብሎት በሰሜን እዝ ስራዊት ከፍተኛ መኮንኖች ላይ ከፈፀመው ርሸና፣ በተጨማሪ የወልቃይት ወረዳ ከተማ በሆነው በማይካድራ ይኖሩ የነበሩ ብሔራቸው አማራ የሆኑትን መርጦ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ በገጀራና በተለያዩ የስለት መሳሪያዎች የሰው እርድ ፈጽሞ ከቦታው ሸሽቷል።

ይህ ከ40 ዓመታት በላይ የዘለቀ የሀገረ ኢትዮጵያ ጥላቻና በተለይም ፀረ አማራ የሆነ ለዘመናት ሲለዝብ ያልቻለ የትህነግ ፋሽስታዊ አቋም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሁሉም ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ብለው በሚያስቡ ወዳጅ ሀገራት ርብርብ ጭምር ተነቅሎ ካልተጣለና ለፍርድ ቀርቦ መፈራረጃ ካልሆነ በስተቀር የእኩይ ተግባር አርአያነቱ ለመላው ዓለም ሰላም ወዳድ ህዝብ በተላይም ለምሥራቅ አፍሪቃና ለቀንዱ አካባቢ ሀገራት እጅግ አደገኛ የሆነ የወንበዴ ስብስብ ነው።

ከላይ የተገለፁት አራት የሰሜን ምዕራብ አማራ (የጎንደር) አካል የሆኑት ወረዳዎችና ከመላው አማራ ዞኖችና ወረዳዎች የተወጣጣ የልዩ ኃይል፣ የሚሊሺያ የፋኖ ኃይል ከመከላከያ ሰራዊት ጋር በመሆን ከፍተኛ የዘመቻ ርብርብ አድርጓል።

ይህም የተቀናጀ የዘመቻ ርብርብ አራቱንም በትህነግ ሰቆቃ ሥር የነበሩትን ወረዳዎች ከትህነግ/ወያኔ ሰው በላ ጥርስ በማውጣት ነፃነታቸውን እንዲያውጁ በደሙ ፋሳሽ በአጥንቱ ክስላሽና በስጋው ቁራሽ ዋጅቶ በሚያኮራ ሁኔታ ተፈጥሯዊውን የነፃነት ምልክት የሆነውን አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅዓላማውን ተክሎ ለማውለብለብ የበቃ የኢትዮጵያዊነት ምሳሌና የህዝብ መከታ መሆኑን ያልመሰከረ ህዝብ ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ መንግስት ቁጥጥር ሥር ባሉና በባለተራው ጠቅላይ ሚኒስትር አንደበት ሳይቀር በጦርነቱ ድል እንደተገኘ መግለፃቸው በጎ ነገር ሆኖ ሳለ ነገር ግን አሁንም እንደበፊቱ የፋሽስት ትህነግ (Political Geography) የመሬት ወረራን በሚያስታውስ ብቻ ሳይሆን ህጋዊ በሚያስመስል መልኩ ምዕራብ ትግራይን ነፃ አውጥተናል ብሎ መናገር ለዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ከእንቅልፋ ያልነቃ በቅዠት ውስጥ ያለ ሰው ወይም ሚዲያ የሚናገረው እንጂ ባለፉት በርካታ ዓመታት መራር ትግል የተካሄደበትና እጅግ የላቀ መስዋዕትነት የተከፋፈለበት መሆኑን መካድና አሁን በማይካድራ የተጨፈጨፉትን ከ500 (አምስት መቶ) በላይ ንፁሀን ያልታጠቁ ሕፃናት፣ አረጋዊያንና ሴቶችን ደም ደመ ከልብ የሚዳርግ አካሄድ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ከላይ ተጠቀሱት ወረዳዎች ተወላጆች ጭምር እንደምናውቀው ከ32 ዓመታት በፊት ትህነግ ኢህአዴግ ወረዳዎቹን ወደ ራሱ ክልል ሲከልል ተቃውሞ ያነሱትን ታላላቅ የአካባቢው ነዋሪዎችንና ታሪክ አዋቂ ተከራካሪዎችን በሚዘገንን ሁኔታ ደብዛቸውን አጥፍቶ በኃይልና በጉልበት ያለ ባለቤቱ ህዝብ ፈቃድ የወሰዳቸው ናቸው።

አሁንም ወላድ በድባብ ትሂድና አዲሱ የአማራ ትውልድ በልዩ ኃይል፣ በሚሊሺና በፋኖ ራሱን አደራጅቶ ከሀገር የመከላከያ ሰራዊት ጋር በመሆን በደሙ ዋጅቶ በጉልበቱ ነፃ ያመጣውን ርስቱን መልሶ ምዕራብ ትግራይ ብሎ መጥራት የህዝቡን መስዋዕትነት መናቅ ብቻ ሳይሆን የትህነግ ዓይነት አማራ ጠልነትና ደምበኛ ጠላትነት ጭምር ሆኖ ሊታይ ይገባል።

**እኛም እንላለን፡- ከ"ባምብሎ በመለስ ተከዜ በፈሰሳ" ወይም ከተከዜ ወዲህ ማዶ ትግራይ አንድ ስንዝር ቁራሽ መሬት የላትም!**

**የህዝቡ የደም መስዋዕትነት ይከበር!**

***ወደ ማይጠፋ እሳት ከመሄድ ቆም ብለን በማሰብ ስለእውነት እንናገር። እውነትንም እንተግብር።***

***ሀገራችን ኢትዮጵያ በቆራጥ ታጋይ ልጆቿ ያላሰለሰ ጽናትና የትግል መስዋዕትነት ወደ ቀደም ሰላሟ፣ እንድነቷና ክብሯ ትመለሳለች!***

***ኢትዮጵያንና ልጆቿን እግዚአብሔር ይባርክ !***

# ፅንፈኝነትና የአማራው እልቂት



**ዶ/ር ብርሃኑ ዘለቀ**
በኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ የከተማ ልማት ፋኩልቲ መምህርና ተመራማሪ

**ብሔር ምንድን ነው?**

ፅንፈኝነት የራስን ማንነት ከሌላው አግዝፎ የማየት አባዜ ነው፡፡ ስለ ብሔር ምንነት በተለያዩ ዘርፎች ያሉ ምሁራን የተለያዩ ትርጓሜ ቢሰጡትም ጠቅለል ባለ መልኩ "ብሄር ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የባህል አዉታሮች/elements ማህበረሰብ/ህዝብ ከአካባቢዉ ፎሪ የሚለይባቸዉና የሚቀበላቸው መገለጫዎች ያሉትና የራሱ የሆነ ግዛት ያለዉ ወይም የሌለዉ ነዉ"። ለምሳሌ የአንድ አካባቢ ህዝብ፣ አንድ አገር ህዝብ፣ የአንድ አህጉር ወይም አለም ዉስጥ ያለ አንድ ህዝብ

ምሳሌ፣ የአማራ ህዝብ በመላዉ ኢትዮጵያ፣ በአፈሪካና በአሁም ያሁዉ በአማራ ማንነቱ የሚያምን ህዝብ ሁሉ ማሁት ነዉ። ይህ ህዝብ ከሌሎች ብሄሮች ጋር በመሆን ከ3 ሺህ አመት በላይ ሀገርንና መንግሥትን መስርቶ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከቅኝ ገዡዎች አስከብሮ የኖረ ነባርና ሀገርን መስርቶ ለትዉልድ ያስረከበ ህዝብ ነዉ። ይህ ህዝብ አባቶቹና እናቶቹ መስርተዉና አስከብረዉ ከትዉልድ-ትዉልድ የተረከባትን ኢትዮጵያ በህሊናው ማህተም አድርጎ ከዚህ በወረደ በመንድርተኝነት ወይም በሌላ ቡድንተኝነት ማሰብም ሆነ መደራጀት ስነ ልቦናዊና ሰብዓዊ እሴቱ ይታገለዋል፤ ፤ያሸንፈዉና አይቀበለዉም።

የብሄር ጨቋኝ-ተጨቋኝ የዉሸት ትርክት ከበዉ የተነሱት ወያኔ፣ ሻቢያና ኦነግ አቆጥቁጠዉ በ1983 ዓ.ም. ወደ ስልጣን መጡ። በ7 አመቱ የወያኔ-ሻቢያ የጫጉላ ዘመንም ሆነ በቀሪዉ የወያኔ ዘመን፣ ጠላት ባማለት እየመረጡና ለይተዉ በአማራ ህዝብ ላይ በደል፣ ዘር ማጥፋት፣ ጭፍጨፋ፣ ወንዶችና ሴቶች እየገደሉ በየጫካዉ ለአውሬ ሰጥተዋል፡፡ ብዙ ዘግናኝ ኢ. ሰብዓዊ ድርጊቶች ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በዚህ ህዝብ ላይ ፈፅመውበታል። ለምሳሌ፣ በ1984 ዓ.ም 12 ሰወች ሌባ፣ ነፍሰ ገዳይ... በሚል ሰበብ ተይዘዉ ያለምንም ፍርድ መገደላቸውን አውቃለሁ፡፡

ከ7 አመታት ስዉር የሻቢያና እሱ የፈጠራቸዉ ኢትዮጵያን የሚመሩ ወያኔዎች የማጎሳቆል፣ የማፈራረስና የዘረፋ ስራቸዉን ሳይጨርሱ ያላሰቡትና ያልጠበቁት የፖለቲካ ፀብ ገጠማቸዉ። የፀባቸዉ ዋና ምክንያት የወያኔ መሪ የነበሩ ከፌዴራል መንግሥቱ እዉቅናና ፈቃድ ዉጭ የፍተሻ ኬላና ቀረጥ የማስከፈል ስራ በነፃ እንድትዘርፍ የተፈቀደላትን ኤርትራን መጀመራቸዉ ነበር። በዚህም ቀረጥ አንከፍልም በማለት የጫኑትን ጭነት (ቡና፣ ጤፍ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሽንኩርት...) እየደፉና እያራገፉ ባዶ መኪና ይዘዉ አገራቸዉ ገቡ። በዚህ ወቅት በዲፕሎማሲ የኢትዮጵያ መሪዎች የሻቢያ ምልምልና ተወካይ መሆኑን እያወቁ፣ የሻቢያ መሪዎች ኤርትራ በትግራይ ክልል ለመቀረጥ የተደረገዉን ሙከራ ሲሰሙ የሀይል አማራጭን ብቻ ወሰኑ። ከኤርትራ በተቃራኒ፣ ኢትዮጵያ ሰራዊቷን የደርግ ነዉ በሚል ሰበብ በትና ነበር።

ከብዙ ግፊት፣ጊዜና ጉትጎታ በኋላ የኢትዮጵያ ሰራዊት እንደገና እንዲለቀምና እንዲደራጅ ተደርጎም በወታደራዊ አመራር ሴራዎች ወደቀ። ጥቂቶችን እንጥቀስ፡-

1. በአደገኛዉ የፈንጅ ዞን በእንስሳትና በሌሎች ወታደራዊ ዘዴዎች ማምከን ሲቻል በሴራ የብዙዎች የሰራዊት አባላት ህይወት ተሰበረ፡፡ 2. ሂያጠቃ አቁም፣ አልፎ ሲገሰግስ ተመለስ የኤርትራ ሉዓላዊ ግዛት ነዉ እየተባለ ብዙ ህይወት አስከፈለን፡:

3. በሰራዊቱ ዉስጥ አስመራን እንይዛለንና ቀይ ባህር እንመለሳለን ብለዉ ያዘዙና የተናገሩ መኮንኖች ጦርነቱ እስኪያበቃ በስር ቤት እንዲቆዩ ተደርገዋል፡፡

4. በተለያዩ አዉደ ዉጊያዎች የኢትዮጵያ ሰራዊት ሲያጠቃ ተመለስ እየትባለ እንዲደመስስ ተደርጓል። በዚህ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የአማራ ወጣቶች እንደተሳተፉና እንደተሰዉ ይታዎቃል።

4. <የቲም ለዉጥ› የተባለዉ የኦሕዴድ-ብሌፅግና ተረኛ ቡድን በዚህ ቡድን በሶማሌ፣ በጋምቤላ ዜጎች የተጨፈጨፉ ቢሆንም በአማራ ህዝብ ላይ በዚህ አጭር ጊዜ የተቀነባበረ ተደጋገሚና ታይቶ የማይታወቅ ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ተፈፅሞበታል። ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ፡-

ሀ/ በ2010 በለዉጡ ሰበብ በጅግጅጋ የብዙ ቤተ ክርስቲያናት መቃጠልና የብዙ (ክርስቲያን አማሮች የዘር ጭፍጨፋ)

ለ/ በአዲስ አበባ ዙሪያ በስንዳፋ፣ ሱሉልታ ... እና በአዲስ አበባ ለዘመናት ከኖሩበት ማፈናቀል

ሐ/ በቡራዩ ኦነግን ሆመቀበሌ በመጡ ቄሮዎች ጋሞዎችና አማሮች መጨፍጨፍ

መ/ የአዲስ አበባ ኗሪዎች በቡራዩ በግፍ ለተጨፈጨፉ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡትን በመግደል ጦላይ ጦር ማሰልጠኛ መታሰራቸዉ

ሠ/ የጃዋር የዉሸት ተከበብሁ ጥሪና ጉዳዩ የማይመለከታቸዉ አማሮች በኦሮሚያ መታረድ

ረ/ በተለያዩ የዉጭ ከተሞች (ካይሮ ሰልፍ፣ በአሜሪካ...) በሚደረጉ ሰልፎች በምስጢር ቁሮ ወከባና ድብደባ መፈፀሙ

ቀ/ በደንቢዶሎ የአማራ ተማሪዎች ተለይተዉ መታገትና መጥፋት በ/ በሀጫሉ መገደል ሰበብ በብዙ የኦሮሚያ ቦታዎች (በዝዋይ፣ ሻሸመኔ፣ አሳሳ፣ በባሌ ሮቤ፣ ባሌ ጎባ፣ በአዲስ አበባ፣...) የዘር ማጥፋት መፈፀሙ

ተ/ በመተከል በአማራነታቸዉ የሴት ነርሶች ሁ. ኑገት

ቸ/ በጉሩ ' ሮዳ የተፈፀመዉ የዘር ማጥፋት

ኀ/ በምዕራብ ወለጋ ተሃሥህሬፐ ቤፐ ውስጥ ንፁሀን አማራዎችን ሰብስበዉ የዘር ማጥፋት መፈፀም

ነ/ በመቀሌ የጦር አዛዦችን (ከ300 በላይ የጦር መኮነኖች)ና ብዛት ያላቸዉ ወታደሮች በራሳቸዉ ወያኔ-ኦነግ በአማራ ጓደኞቻቸዉ ላይ በኢሰብዓዊነት፣ በግፍና አሰቃቂ በሆነ አገዳደል (ለ3 ቀን ያለዉሀና ምግብ በማሰቃየትና ባዶ እርቃናቸዉን የፍጥኝ አስረዉ) የዘር ማጥፋት መፈፀማቸው፡፡

እዚህ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎችን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡

1. የአማራ ተወላጅ የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ለምን በጭካኔና በዘግናኝ ሁኔታ እንዲገደሉ ተደረገ?

2. የ3 ቀናት ረጅም ጊዜ ግድያና አሰቃቂ ድርጊት በመከላከያ ላይ ፈፅመዉ ወደ ጎንደር እስኪገሰግሱ ሁለም አካል ለምን ጆሮ ዳባ ልበስ አለ?

3. ከሀገሪቱ መከላከያ የተላኩት አመራሮችና የጦር አዛዦች በትግራይ ልዩ ሀይል ተከበብን ብለዉ ሲመለሱ ለምን መዋጋት አቃታቸው?

4. በማይካድራ ከተማ ከ600 በላይ ንፁሃን በአማራነታቸዉ በወያኔ-ኦነግ ወታደሮች የተጨፈጨፉት ከሳምነት በፊት ትግሬኛ ተናጋሪዎችን ከከተማ አዉጥተዉ ታቅዶና ታስቦበት የተፈፀመ ነው፡፡ ይህ ሲሆን መከላከያና መንግስት አያዉቁምን?

5.ትነግ-ኦነግ ለምን በአሁኑ ወቅት የአማራን ህዝብ ለይተዉ የዘር መጥፋት ያደርሱበታል?

**አማራ ለምን ተለይቶ የዘር ማጥፋት ይካሄድበታል?**

1. <የብሄር ጭቆናን ያመጣብን አማራ ነዉ› በማት በዉሸት ትርክት ኢትዮጵያን ማፈራረስ የሚመኙ ፅንፈኞች ወደ ስልጣን ስለመጡ 2.የአማራነት ስነ ልቦና፣ ስብዕና ከኢትዮጵያዊነት ማማና ፍቅር ላይ በመሆን የመንደርተኛና ፀረ-ኢትዮጵያ አስተሳሰብ ያላቸውን ስለሚቃረን

3. የመንግሥት ስልጣን ከመንደርተኛ ወያኔ ወደ ሌላ መንደርተኛ ያለ ገለልተኛ የፍትህ ተቋማት መተላለፉ

4. ኢትዮጵያን መስራች አማራ በመሆኑ መስራቹን ካላጠፋን ኢትዮጵያን መከፋፈልና መገነጣጠል አንችልም ብለዉ ስለሚያምኑ

**በኢትዮጵያ ውስጥ የዘር ፍጅትና ግጭትን ለማጥፋት ምን ይደረግ?**

1. ሀገርን ለማፍርስ በዉሸትና በብሄር ጥላቻ ላይ የተሰራዉን ሕገ መንግሥትና የዘር ፌዴራሊዝሙን ወደ ልማታዊና የተሻለ አስተዳድራዊ መሰረት የሚሆን ሕገ መንግሥትና ፌዴራሊዝም መቅረፅ

2. ለእዉነተኛ ዴሞክራሲና ለህዝብ ልዕልናና ተወዳዳሪ ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚሠራ መንግሥት እንዲመሰረት መታገል

3. ፅንፈኞች የሚያደርጉትን ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለማፍረስ የከፈቱትን ዘመቻ ለማስቆም በመተባበር መስራት

4. ምሁራን ዝም ከማለት ወጥተዉ በኢትዮጵያ ወደ ብሄራዊ መግባባት እንዲመጣ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።



# ‘እውነት’ የመንግሥት የግል ንብረቱ ነችን?

በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ገዥዎች ያሉት እውነት፤ ከእነርሱ በተቃርኖ የተነገረው ደግሞ ሀሰት ተደርጎ ሲተረክ ቆይቷል። እንደ አብይ አሕመድ ስብስብ ግን ውሸትን መለያው ያደረገ ሥርዓት የለም ማለት ይቻላል። በማጭበርበር ስልት ወደ ሥልጣን የመጡት ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አሕመድ አሁንም ውሸትን ዋነኛ የአገዛዝ ስትራቴጂያቸው አድርገውት ቀጥለዋል። የፍትሕ ስርዓቱማ ልብወለድ ፀሃፊ የሀሰት ፋብሪካ ሆኗል። የእነ እስክንድር ነጋን የሽብር ክስ የፃፈው ዐቃቤ ሕግ ተብዬ የልብ ወለድ ደራሲ ቢሆን ወፍራም እንጀራ ያገኝ ነበር። በርግጥ አሁንም እንጀራ አላጣም። ነገር ግን ይህኛው እንጀራ ነገ መንግሥት ሲገለበጥ አብሮ በአፍጢሙ ይገለበጣል። ለመሆኑ እውነት ምንድን ናት?

ማንም ፈጻሚ ማን ሐሰት፤ ሐሰት ሆና ትኖራለች፤ ባሕሪዋ ነውና። በአንጻሩ እውነትም እንዲሁ።

የፈጻሚዋ ማንነትም ሆነ ምንነት ሥሕተትን ልክ /ትክክል/ ሊያደርጋት የሚችል /የሚያስችል/ አንድም ኃይል እንደሌለ መታወቅ ይኖርበታል።

የፈጻሚዋ ማንነት ሥህተትን ልክ የሚያደርጋት ከሆነ ሥህተት ልክ መሆኗ ሳይሆን ሥህተት የሚታይበት መነጽር እና የህሊና እይታ ነው የተዛባ፣ የተወለጋገደ እና የተምታታ የሆነው እንጅ ሥህተት ልክ ሆኖ /መሆኑ/ አይደለም።

ሥህተትን በተገቢው ቋንቋ ገላጭ ሥሙ ሥሕተት ተብሎ መጠራት አለበት። ምንም ማሽሞንሞን እና ጫጉላ ቤት እንደገባች ልጃገረድ መሽኮርመም አያስፈልግም።

ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ፕሬዘዳንት፣ ፓስተር ሆነ ፕሮፌሰር… ከያኒ ሆነ ባለ ንዋይ፣ አትሌት ወይም ባለ ዝና መሆን ከላይ ከተጠቀሱት ካንድም ሆነ ከሌላው ጋር አብሮ መቆም ወይም መንጎድ እንጂ ማንነታቸውን ገሽልጦ ጥሎ አዲስ ማንነትን የመስጠትም ሆነ የማጎናጸፍና ወይም የመለወጥ ኃይልና ሥልጣን ማንም የለውም። “አካፋ አካፋ ነው። ዶማም ዶማ”

ብርሐን ብርሐን እንጅ ጨለማ ሊሆን እንደማይችል ሁሉ እውነትም እውነት እንጅ ውሸት ላይሆን ግድ ነው።

“ምንም ጌታ ብትሆን ጌታ ቢወልድህ አገርህን ግዛ እንጂ ልቤን ማን ቢያገድህ።” ስትል… እንዳዘመረችውዋ እንዲሁ ይሉታል እንጅ በጭራሽ አይሰሙትም። ከብርም አይሰጡትም።

ወታደሩን ጭፍራውን አድናቂውን ሊያስማራ ሊያዝ ይችል ይሆናል በሕግ የማስከበር ሽፋን ካባ ሥም የሚተወን ክህነትና ብቃት እንኳ የማይታይበት ትወና ቢተወንም እንኳ፤ የእውነትንም ሆነ የሐሰትን ተፈጥሯዊ ማንነታቸውን የማስለወጥ አቅም ሊኖረው አይችልም። ለእርሱም የሚታዘዙ አይደሉም። ትዕዛዙንም ሠምተው የሚተገብሩት ሊሆኑ አይችሉም። በተደነገገላቸው ድንጋጌ የእራሳቸውን ማንነት እና ይዘት ጠብቀው ከመትመም በቀር።

ከእውነት ጋር የቆመ እውነተኛ ከውሸትም ጋር ደግሞ ያበረ ከሆነ ውሸተኛ /ውሸታም/ ነው። በካምፓሎጅ ውስጥ እንደሚከናወን የኳስ ግጥሚያ ጨዋታ በቲፎዞ እና በስሜት በጩኸት እና ጫጫታ የእነዚህን ነገሮች ባሕሪያዊ ይዘት እና ማንነት ሊቀየር ወይም ሊያስቀይር የሚቻልበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም።

ይኼንን የተፈጥሮ ሕግ ለማሽነፍ መውተርተር እና መፋደስ፣ ጭፍራን በማብዛት እና ማሊያ በማልበስ፣ በሆታና ሁካታ በጭብጨባም ሆነ በአፈሙዝ፣ በጥቅማጥቅም በማነሁለል እና በማፍዘዝ ወይንም በበሬ ወለደ የፈጠራ ትርክት እንዲሁም በባለ ተረኝነት የበታችነት ቅዠት ተውሳካዊ ልክፍን በመነዳት፣ በመናወዝ ወዘተ ለማምታታት ለማሸነፍ እና ዝም ለማሰኘት መሞከር የግል ምርጫ እና ይዞታ ውስጥ ያለ ውሳኔ ቢሆንም ውጤቱ ግን ተራራን የመገፋት ያህል የማይቻል ነው። የጊዜ ጉዳይ እንጅ መራራ ሽንፈት እንደሚያስከትል ከታሪክ መማር በተቻለ ነበር።

በዓለማችን ታሪክ የከተባቸው በሠራዊታቸውና በፈረሶቻቸው ብዛት እና ድርጅት፣ በሃብታቸው በሥልጣናቸው በዝናቸው ታውቀው ገንነው ተከብረው እና ተፈርተው እንዲሁም ዓለምና ሠላሟን ያሸበሩ እና ያንቀጠቀጡም፣ የነጠቁም አያሌ ነበሩ።

መንግሥታት መሪዎች ተነስተዋል። ጠፍተዋልም። በወቅቱ የገነኑ የሚመስላቸው የነገ እንደ ትናንትቶቹ ሁሉ ትቢያና ቡናኝ መሆናቸውን ዛሬ ላይ ሆነው ለመገንዘብ ዓይነ ልቦናቸው ባልጠግብ ባዩ የተረኝነት ስካር ተይዟል።

ቅራቅንቦን የማግበስበስ… ሁሉ የኔ ለኔ በኔ “እኔ ከሞትኩ የስርዶ አይብቀል” አባዜ። እንደሠጎኑዋ እራሷዋን በአሸዋ ውስጥ የማስረግ መላ አካሏን ደጅ አድርጋ ከአዳኝዋ እራሷን የሰወረች እንደመሰላት የወፍ ዝርያ እንጪጭ የሞኝ ብልጣብልጥነት ዘዴ ዓይነት ነው።

የሆነው ቢሆንም ከሁሉ በፊት በጽድቅ የሚበይነው የእውነት አምላክ ሁሉን ያያል። ለጥቆም እርሱ ባዘጋጀው ወቅት ታሪክ ግዜ እና ሕዝብ በራሳቸው ሠዓት ችሎት መዋላቸው አይቀርም። ለሁሉም እንደዘሩት ዘር ፍሬን መሰብሰባቸው የተፈጥሮ ሕግ ነው።

ለሁሉም የተገባቸውን ቦታ በወቅቱና በግዜው ሰጥቷቸዋል። መስጠቱንም ይቀጥላል። “ከጸሐይ በታች ለሆነው ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።” ያንን ጊዜ ማን ነው እርሱ? የትኛው ባለጉልበት ነው? የትኛውስ ባለተራ ነው ይኼንን ከመፈጸም ተገዳድሮ ሊቀለብስ የሚችል?

ግንብን በመገንባት የከፍታቸውን ጥግ ከሠማያዊው መንግሥት ጋር ለማፎካከር እንደታተሩት የባቢሎኗ ናምሩድ? 7 ዓመት እንደኮበት ግጦሽ ሳር ቀለቡ እንደሆነው የፐርሺያው ናቡ ከደነጾር? አልታዘዝም። አሻፈረኝ በማለት እስራኤላውያንን አለቅም ብሎ ከመለኮት ኃይል ጋር በመፋጠጥ እራሱን ሕዝቡን እና አገሩን በመቅሰፍትና በመዓት እንዳስመታው የግብጹ ፈርኦን? የተዋጋውን ጦር ሁሉ አሸንፎ የምገጥመው አጣሁ ብሎ በጦር ድንኳኑ ውስጥ ተቀምጦ ተንሰቅስቆ እንዳለቀሰው እና በመጨረሻም ፍልስልሱ እንደወጣው የግሪኩ ኃያል ጄነራል አሌክሳንደር? በፈረንሳይ አብዮት ውስጥ…በጉልበት ወደ ሥልጣን እርከን በመሰቀል የንግሥናን በትረ ሥልጣን ተቆጣጥሮ አውሮፓን የጦርነት ቀጠና እንድትሆን ያደረጋት እንደ ፈረንሳዩ ቀዳማዊ ናፖሊዮን…? እንዲሁም ከ6 ሚሊዮን እስራኤላውንያንን እና ወደ 5 ሚሊዮን በላይ ሌሎች ዘሮችን ለማጽዳት ለተከናወነው አስቀያሚ የዘር ፍጅት የጥፋቱ ዓላሚና አስፈጻሚ የነበረውና የጀርመንን የበላይነት በዓለም ሕዝብ እና መንግሥታት ጫንቃ ላይ ቀንበሩን ለመጫን የዳከረው የዘረኝነት ጭራቁ አዶልፍ ሒትለር? ወዘተ በማንሳትና እና በመዘርዘር መራንህ ለሚሉት ሕዝብ፤ አስተዳድርንህ ለሚሉት አገርና ግዛታቸው ላይ ያደረሱትን ቀውስ፣ ትርምስ እና ውድመት በማንሳት ብዙ ማለት ይቻላል።

ነገር ግን የቱንም ያህል በጉልበት ቢጎለበት፣ በተክህኖ ቢካኑት፣ በእውቀትም ቢታቆቱት በብልጽግናም ቢበለጽጉ፤ ደረስንበት ጨበጥነው በሚሉት የስኬት የከፍታ እርከን ላይ ቢንጠለጠሉ፤

ዛሬም ጸሐይን ማለዳ ብርሐኑዋን ለመፈንጠቅ ከመውጣት እና በምሽትም ከመጥለቅ፣ አራቱንም ወቅቶች በግዜያቸው ከመግባትና በግዜውም ለሌላው የመልቀቅ ሂደታቸውን ሊያቆማቸው፣ ሊያስተጓጉላቸው ወይም ሊገታቸው የቻለ እና ለችልም የሚችል አንድም መልከአምድራዊ ኃይል ወይም ጉልበት አልነበረም። የለምም ሊኖርም አይችልም።

የተፈጥሮን ህግ ሊያፋልስ፣ ሊያዛንፍ የቻለና የሚችል ምድራዊ ጉልበት ወይም ኃይል እንደሌለ ሁሉ ሐሰትንም ልክ፣ እውነትንም ውሸት ብርሃንን ጨለማ አድርጎ መቀየር የሚቻለው ማነው እሱ? የትኛው ነው? ወዴት አለ? አንድም

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# “ገበታ ለሀገር” - ከዶሮና ዓሳ ወግ አንጻር

ከማለፊያ ደርሰህ

ዶሮና ዓሳ የቀረበ ገበታ አይተው ወግ ይጀምራሉ:: በገበታው ላይ የቀረበው ምግብ የዕንቁላል ጥብስና ዓሳ ነው:: ዶሮው “ይህ ገበታ ጣፋጭ ሆኖ ትላልቅ መሳፍንትና መኳንንት ተደስተው እንዲመገቡ ለማድረግ የእኔ አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው:: ምክንያቱም እንቁላሉን የጣለችው ሚስቴ ዶሮ ነች፤ እንቁላሉ የሁለታችንም ዶሮዎች አበርክቶ ነው” ብሎ ተኩራራ::

ዓሳውም ተደንቆ “እናቱ የሞተችበትና ገበያ የሄደችበት እኩል ያለቅሳሉ” ብሎ ተረተና “ሰማህ ዶሮ፣ ገበታው ላይ ካለው ምግብ አንዱ ከዶሮ የተገኘ ዕንቁላል መሆኑ እርግጥ ነው:: ገበታው ላይ የቀረበው ዓሳ ግን እኔ ታርጄና ተበልቼ የቀረበ የእኔ አካል ነው::እኔ ነኝ” ብሎ ተናገረ::

ይህ የዶሮና የዓሳ ታሪክ በጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ አህመድ (ዶክተር) የቀረበውን “ገበታ ለሀገር” አስታወሰኝ::

የጽሑፌ ዋና ጉዳይ ግን ጠቅላይ ሚንስትሩ በ”ገበታ ለሀገር” ለመገንባት ላቀዷቸው የወንጪ፣ የጎርጎራ እና የኮይሻ ፓርኮች ግንባታ ከመንግሥት ሠራተኞች የአንድ ወር ደመወዝ መቆረጡን የተመለከተ ነው:: በሦስቱም ቦታዎች የሚገነቡት ፓርኮች ለቱሪዝም፣ ለኢኮኖሚ፣ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና ለሌሎችም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች እንደሚጠቅሙ አያከራክርም:: ዋናው ቁም ነገር ግን አሁን በበርካታ ችግሮች ለምትጠበሰው ሀገራችን ከዚህ የሚቀድሙ መሠራት ያለባቸው አጣዳፊ ጉዳዮች የሉም ወይ? የሚለው ነው::

ሀገራችን በዘረኝነት መርዝ በተዘራው ጎጠኝነት የተነሳ ሰው ውሎ መግባቱ አሳሳቢ በሆነበት፣ በበርካታ የሀገራችን ክፍሎች የበረሃ አንበጣ መንጋ ሰብል በማውደም ላይ ባለበት፣ የኑሮ ውድነቱ “ውድነት” በሚለው ቃል ሳይሆን እንደ “ሰደድ በሚንበለበል እሳት” በተመሰለበት፣ የብር የመግዛት አቅም ቀኑ እንዳለፈበት እንደ ትናንት ጋዜጣ ዋጋ ባጣበትና ገበያው በሳጥናኤል የሚመራ በሚመስልበት በዚህ ወቅት “ገበታ ለሀገር” አንገብጋቢ ሀገራዊ አጀንዳ ነውን?

በኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ሁኔታ በመጠቃት ላይ ካሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የመንግሥት ሠራተኛው አንዱ ነው:: በማይመጥን ዝቅተኛ ደመወዝ በስቃይ የሚኖረው የመንግሥት ሠራተኛ ከዓመት ዓመት ከድኅነት ወለል በታች እየወረደ የበለጠ ድሃ እየሆነ ነው::

### “ገበታ ለሀገር” - የእናት ሀገር ጥሪ?

ሀገር ችግር ላይ ስትወድቅ ለልጆቿ (ለዜጎቿ) የድረሱልኝ ጥሪ ታቀርባለች:: ከ42 ዓመት በፊት ሀገራችን ያጋጠማትን ክፉ ጊዜ ለአብነት ላንሳ:: ኢትዮጵያ በ1969 ዓ.ም በምስራቅ 700 ኪሎ ሜትር በደቡብ ደግሞ እስከ 300 ኪሎ ሜትር ድረስ በሱማሊያ ጦር በተወረረችና የሰሜን ተገንጣይ ኃይሎች ኤርትራን ለማስገንጠል አስመራና ዙሪያዋን በከበቡት ቀውጢና ፈታኝ ወቅት ሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሚያዝያ 04 ቀን 1969 ዓ.ም “እናት ሀገርህ ተወራለች፤ ተነሥ! ታጠቅ! ዝመት!” ብለው የእናት ሀገር ጥሪ አቀረቡ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪውን ተቀብሎ 300 ሺ ሰው ታጠቅ ጦር ሰፈር በመከተት በአጭር ጊዜ ሰልጥኖ ሰኔ 18 ቀን 1969 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሰልፍ አደረገ:: ወደ ጦር ግንባር ዘመተ:: አበቃላት የተባለችው ኢትዮጵያም የሱማሊያን ጦር ጠራርጋ ከድንበርዋ በማስወጣት አይበገሬነቷን አረጋገጠች:: ዕድሮች፣ የመንግሥት ሠራተኞች በአጠቃላይ ሕዝቡ ጦር ግንባር ለዘመተው ኃይል ደጀን በመሆን ባደረገው ሁለገብ ድጋፍ ያ ክፉ ቀን ታለፈ:: ኢትዮጵያም ከውርደት ዳነች:: በኋላም ከሰሜን ተገንጣይ ኃይሎች ጋር በተደረገው ረጅምና አሰልቺ ጦርነት ደርግ በአዋጅ በማስገደድ የመንግሥት ሠራተኞች የአንድ ወር ደመወዛቸውን በአንድ ዓመት ክፍያ በተደጋጋሚ ዓመታት እንዲከፍሉ አድርጓል::

ሲያልቅ አያምር እንዲሉ ደርግም ወደቀ:: ኤርትራም ተገነጠለች:: ሕወሓትም የዘረኝነት መርዙን በሀገራችን ዘራ:: በ1983 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ በኢትዮጵያ፣ በሻዕቢያና በኢሕአዴግ (ሕወሓት) እና ሻዕቢያ መካከል በአሜሪካዊው ኸርማን ኮህን አደራዳሪነት የሰላም ድርድር ተካሔደ:: ደርግ አብቅቶለት ነበር:: ኸርማን ኮህን ኢሳይያሥ አፈወርቂን አሳምነው አሰብ ለኢትዮጵያ እንዲሆን ድርድር እንዲካሔድ ሲጠይቁ መለስ ዜናዊ “አሰብ የኤርትራ ናት” በሚል ሀሳቡን ውድቅ እንዳደረጉባቸው ኮህን ለተለያዩ ሚዲያዎች ገልጸዋል:: ሕወሓት በዚህ ታሪኩ አለማፈሩ ይገርመኛል:: ታሪክ ይቅርታ በማይደረግለት ስህተት መዝግቦታል::

ሀገርን የተፈጥሮ፣ የጦርነት እና ሌሎች ችግሮችና አደጋ ሲያጋጥማት አንድ ዜጋ እንኳን ገንዘቡንና ሕይወቱን ሊሰጥ የተገባ ነው:: በዚህ በኩልም ኢትዮጵያውያን የሚያኮራ ታሪክ እንዳለን ይታወቃል:: በቅርብ ዘመናት ኢትዮጵያውያን ከማጂ እስከ ጂጂ፣ ከመቀሌ እስከ ሞያሌ፣ ከአሜድላ እስከ ጋምቤላ፣ ከጅጅጋ እስከ ጅጋ፣ ከበደሌ እስከ ቶጎ ውጫሌ፣ ከጠገዴ እስከ ጎዴ፣ ከሁመራ እስከ ሰመራ በአንድነት ያነሳሳቸው ታላቁ የአባይ ግድብ ነው:: የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ለግድቡ በሦስት የተለያዩ ዓመታት የሦስት ወር ደመወዙን ለግሷል:: ልገሳው ወደ ቦንድ እንዲዛወር በመደረጉ ደስተኛ ነው:: ኢትዮጵያውያንን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ያስማማ በኩር ብሔራዊ አጀንዳ በመሆኑ ሠራተኛው ተቸግሮም ቢሆን ደመወዝ በመለገሱ ለሀገሩ ታላቅ ድርሻ አበርክቷል:: በዚህም እንደሚኮራ ይታመናል::

### ዓሳው - የመንግሥት ሠራተኛ

ከካድሬና ካድሬ ቀመስ፣ ከገንዘብ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ካላቸው ሌባ የመንግሥት ሠራተኞችና በ‹ኤክስፐርቲዝነት› ሙያቸው የተሻለ ክፍያ ከሚያገኙ ጥቂት ሠራተኞች በስተቀር አብዛኛው የመንግሥት ሠራተኛ ኑሮው የሰቆቃ ነው:: ምሳቸውን ሳይበሉ የሚውሉ፣ ሲያማቸው እንኳ መታከሚያ በማጣት በሽታቸውን ተሸክመው የሚሰቃዩ ሠራተኞች እንዳሉ ይታወቃል:: ለሠራተኞቻቸው ነጻ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ብቻ ናቸው:: አብዛኛዎቹ ባለ በጀት መስሪያ ቤቶች ለሠራተኞቻቸው ነጻ የሕክምና አገልግሎት አይሰጡም::

ኅብረተሰቡም ቢሆን ለመንግሥት ሠራተኞች የሚሰጠው ክብር ዝቅ ያለ ነው:: በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ በአነስተኛ ደመወዝ ተመግቦ፣ለብሶ፣ቤተሰብ ያለው ቤተሰቡን አስተዳድሮና ልጆቹን አስተምሮ መኖር በአስማት ካልሆነ በቀር እንዴት ይቻላል? ሲያስቡት ያማል::

ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አህመድ (ዶክተር) ወደ ስልጣን እንደመጡ የመንግሥት ሰራተኛ በነጻ የሚያገለግል መሆኑን በመግለጽ ማሞካሸታቸው ይታወሳል:: በወቅቱም የበርካታ መንግሥት ሠራተኞች ተስፋ መብራት ጀምሮ ነበር:: በኋላ ግን በተደጋጋሚ ባደረጓቸው ንግግሮች፣ ለመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ መጨመር የኑሮ ውድነቱ እንዲጨምር ከማድረግ ውጭ የሚፈይደው ነገር የለም በማለት ተናግረዋል::

ጠቅላይ ሚንስትሩ በስልጣን ዘመናቸው ለመንግሥት ሠራተኛው አንድ ሳንቲም የደመወዝ ጭማሪ አላደረጉም:: ቀደም ሲል በባለበጀት መስሪያ ቤቶች የሚሰራ አንድ ሠራተኛ የደረጃ ዕድገት ሲያገኝ ያገኘው ጭማሪ በሙሉ ይከፈለው

ነበር:: ጠቅላይ ሚንስትሩ ከመጡ በኋላ ግን አንድ ሠራተኛ የደረጃ ዕድገት ካገኘ የሚከፈለው ለ3 ተከፍሎ በ3 ዓመታት ውስጥ ነው:: በምሳሌ አስደግፌ እንዳስረዳ ይፈቀድልኝ:: አንድ ሠራተኛ ከሐምሌ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የብር 900.00 ጭማሪ የደረጃ ዕድገት ቢያገኝ የመጀመሪያው ብር 300.00 የሚከፈለው እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም፣ ሁለተኛው ብር 300.00 የሚከፈለው እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም እና ሦስተኛው ብር 300.00 የሚከፈለው እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ነው:: የተጨመረለትን ብር 900.00 በሙሉ የሚያገኘው በሦስተኛ ዓመቱ ነው:: ይህ በዘመነ ብልጽግና በመንግሥት ሰራተኛው ላይ እየተፈጸመ ያለ ግፍ ነው::

በርግጥ መንግሥት፣የመንግሥት ሠራተኛውን ኑሮ ቀዳዳ ሁሉ የሚሞላ የደመወዝ ጭማሪ የማድረግ አቅም እንደሌለው ይታወቃል:: የኑሮ ውድነቱ መነሻና መድረሻ መፍትሔ ለመንግሥት ሠራተኛ ከሚጨመር የደመወዝ ጭማሪ ጋር አይገናኝም:: በምጣኔ ሀብት ባለ ሙያዎች ዘንድ ለዋጋ ግሽበት መንስዔና መፍትሄ ቁልፉ ጉዳይ "የፍላጎትና የአቅርቦት መጣጣም" እንጂ ለመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ የመጨመርና ያለመጨመር ጉዳይ አይደለም:: ደመወዝ ሳይጨመርም በብርሃን ፍጥነት የዕቃዎች ዋጋ ግሽበት ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይታይም::

በዚህም አንጻር "በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ" እንዲሉ በ"ገበታ ለሀገር" ስም አብዛኛው ሠራተኛ ሳያምን በካድሬ አደረጃጀት የአንድ ወር ደመወዙን እንዲሰጥ መደረጉ የመንግሥት ሰራተኛን ደመወዝ እንደመንጠቅ ይቆጠራል::

የመጣው ሥርዓት ሁሉ ጉልበቱን የሚፈትሸው በመንግሥት ሠራተኛው ላይ ነው:: የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር የመንግሥት ሠራተኛው የግልገልና ዋና ካድሬዎች የስብሰባ ማድመቂያ፣ንግግር መለማመጃ፣በአግባቡ ያልተኮረጁና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያልተዛመዱ ፍልስፍናዎች መሞከሪያና በስሙ የሚነገድበት የኅብረተሰብ ክፍል መሆኑ ነው::

በዘመነ ሕወሓት ሥራ ለመቀጠር፣በሥራ ላይ ዕድገት ለማግኘትና የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ለማግኘት መስፈርቱ በወንዝ ልጅነት መጠቃቀም፣ ጎጠኛ መሆንና በጎጠኞች መረብ ስር መሆን ነው:: ይህን ያደረገ ካድሬ ሹም ይመሰገናል እንጂ አድሎ እንዳደረገ አይቆጠርም:: ይህ ክፉ ሥራ በዘመነ ብልጽግና ተጠናክሮ በመቀጠሉ "ዓሳው - የመንግሥት ሠራተኛ" እንደ ዶሮው እንቁላሉን ሳይሆን ራሱን እየሰጠ እየተበለተ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው::

## ዶሮው - ካድሬ ሹም

"መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ" እንዲሉ ብልጽግና ፓርቲ የቀድሞው ኢሕአዴግ ቁጥር 2 ነው:: ከኢሕአዴግ ላይ ሲቀነስ ሕወሓት፤ ሲደመር አጋር ድርጅቶች (ኢሕአዴግ - ሕወሓት + አጋር ድርጅቶች) ማለት ነው::

ሕወሓት የበጋ መብረቅ ወርዶበት ሳያስበው ከአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ከተባረረ ማግስት ጀምሮ ሕወሓትን የተኩት ከተላላኪነት ያለፈ ሚና ያልነበራቸው ያሳደጋቸው ተላላኪዎቹ ከእሱ ብሰው ተገኝተዋል:: የታዘብነውም ተተኪዎቹ ይሉኝታ የሌላቸው፣ በጎሳ ፍቅር ያበዱ፣ከብሔራዊ ልማትና ከብዙኃን ፍላጎት ይልቅ የግል ስልጣንና ሀብት በማካበት ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ነው:: የሕወሓትን "ተራራ ማንቀጥቀጥ" ገድል የማስተጋባት ተግባር ፈጽመው አሁን ደግሞ ብልጽግናን የማጋነን ዘይቤ የጀመሩት የትናንቱ ካድሬዎች መርሕ አልባ በመሆናቸው ፈጥነው የሚሰለፉት ከአሸናፊዎች ጋር እንደሆነ ይታወቃል::

አብዛኛዎቹ ካድሬ ሹማምንት ከሁሉም በላይ ራሳቸውን የሚያስቀድሙ፣ የሾማቸው አካል ፊቱን ካጠቆረባቸው የሚኖሩበት ቪላ ቤትና ኮብራ መኪና ሲነጠቁ እየታያቸው ሌት ተቀን የሚቃዡ እንጂ በራሳቸው የሚተማመኑ አይደሉም::

እነዚህ ካድሬ ሹማምንት በኅብረተሰቡ ውስጥ የተሻለ ኑሮ የሚኖሩ፣ መንግሥት ማለፊያ ቤትና ምርጥ መኪና የሰጣቸው፣ የተሻለ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ያላቸው፣ በውጭ ሀገር ጉዞ ዶላር የሚሰበስቡ እና ኢመደበኛ በሆነ ዘዴም መሬቱን እና ገንዘቡን የሚሰበስቡ ናቸው:: ጠቅላይ ሚንስትሩንና እሳቸውን የከበቧቸውን ለማስደሰትና "ንሴብሆን" ለመሻማት እሽቅድምድም ውስጥ ገብተዋል:: እነዚህ ባለስልጣኖችና የብልጽግና ካድሬዎች ለ"ገበታ ለሀገር" የወር ደመወዛቸውን ቢሰጡ እንደ ዶሮው እንቁላሉን ሰጡ እንጂ እንደ ዓሳው ራሳቸውን አልሰጡም::

በሀገራችን እየተለመደ የመጣው አንድ ባለስልጣን በጎሳ ሰንሰለት ውስጥ እስከታቀፈና የፖለቲካውን ቀይ መስመር እስካላለፈ ድረስ የፈለገውን ቢያጠፋ ጠያቂ የሌለው መሆኑ ነው:: አጥፍቷል ተብሎ ቢነሳም ሌላ የተሻለ ወንበር ላይ ይቀመጣል እንጂ ተጠያቂ አይሆንም:: ከዚህም አንጻር የመንግሥት ሠራተኛውና ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል እንደ ዓሳው ራሱን እየሰጠ ካድሬው ሹም ደግሞ እንደ ዶሮው ዕንቁላሉን እየሰጠ በሹመት ላይ ሹመት እየጨመረ ዕድሜውን ይገፋል::

በመጨረሻም ዐብይ አህመድ (ዶክተር) በኑሮ ውድነት ከቤተሰቡ ጋር በመሰቃየት ላይ የሚገኘው የዓሳ ተምሳሌት የሆነውን የመንግሥት ሠራተኛ "ገበታ ለሀገር" በሚል ሰበብ የሚቆረጥበት ሙሉ ደመወዝ በፍጹም አግባ አለመኾኑን ሊረዱት እንደሚገባ መልእክቴን አስተላልፋለሁ::

# 'እውነት' የመንግሥት . . .

*ከገፅ 11 የዞረ*

የለም፡፡ ሊኖርም አይችልም፡፡ ተጠሪነታቸው ለሕግጋቶቹ ደንጋጊ እና አጽኚ ብቻ ነውና፡፡

ስለዚህ ጎበዝ! ከሐሰት ጋር የሐሰት ግብረ በላ ሆኖ ከሐሰተኞች ጋር ተዘንቆ የሐሰትን የጽዋ ብርጭቆ እያንቃጨሉ ከመጨለጥ፤ ከእውነት ጋር በእውነተኞች ጎራ አብሮ በመቆም /የከፋ የመከራ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ ቢታውቅም ቅሉ/ እራስን እንደ ሻማ እያቀለጡ ለሌላው ብርሃን መሆንን መምረጥ እና ዋጋን መክፈል ትልቅ ቋሚና ቁም ነገር ነው፡፡ ከእውነት ጋር ማበር ይሻላል፡፡ የከፍታው መንገድ በእርሱ ውስጥ ነውና፡፡

ሐሰትን እና ሐሰተኞችን እንጠየፍ፤ ኀጢያት በመሆኑ፡፡ ከእውነት ጋር እንቁም እንራባት፣ እንጠማትም፡፡ ይህቺ ምድር ከንቱ የከንቱ ከንቱ ናት፡፡ ሃላፊም ጠፊም ናት፡፡ የዛሬ ቋሚዎች የነገ ሙቶች መሆን አለ፡፡ ወደ ማይቀርበት መትመም ይኖራል፡፡ አካላዊ ሞት ብቻ ሳይሆን ታሪኮዊ ሞትም አለ፡፡

የዛሬው ጨቅላ የነገው አገር ተረካቢ ትውልድ ችሎት ፊት መቅረብም መዳኘትም አለ፡፡ ይኸ ሁሉ አቧራ እንደቦነነ አይኖርም፡፡ ይጠራል፡፡

"እርኩም ይኼድና ይኸም ቀን ያልፍና
ወንድም እና ወንድም የሆነ እንደሁ ሥምም
ሽንኩርት በልቻለሁ እኔ ሠው አልስምም፡፡"

ከዚህ በላይ የተቋጠችው ሥንኝ በእብሪተኛው እና ዘረኛው ፋሽስት የጣሊያን አምባገነናዊ አምስት የወረራ ዓመታት ወቅት ልክ እንደዛሬው ሁሉ ከጠላት ዓላማ ጋር አብረው በመቆም ሐገርና ሕዝብን ይገድሉና ያስገድሉ ለነበሩ ሆድ አምላኩ ለነበሩ ባንዶች በወቅቱ ከተቋጠሩ ብዙ ስንኞች መካከል አንዷ ነበረች፡፡ ታዲያ ታሪክ እራሱን ሲደግም ነው አሁንም የሚታየው፡፡

ታሪክና ትውልድ በምን ያስታውሱን ይሆን? ምርጫውን መምረጥና ማስተካከል ዛሬ ነው እርሱም አሁን፡፡ ከብርሐን ከእውነት ጋር አብሮ ለእውነት ዋጋ መክፈልን አለመፍራት፡፡ መቁረጥ ነው፡፡ መጨከን ነው፡፡ ሞት እንደሁ አይቀርም፡፡ በእውነት ፊት ከመዳኘት ግን ማን ያመልጣል?... ፊጣሪ ዓይነ ልቦናችንን ያብራልን፡፡ በቸር ይግጠመን!!!

# የድንጋይ ሸበት

እስኪ ልጠይቅሽ እውቀት ተናገሪ
ገድ ነሽ መሰጠት ወይንስ መርግሪ
ጨለማውን ገላጭ ብርሀን አብሳሪ
የተቆለፈውን ሚስጥርን ሰርሳሪ፤
በዘመን ኹረት ውስጥ ጥበብ አቀባባይ
በትናንቱ በኩል የዛሬውን ሁነሽ የነገን የምትስይ
በዘመን ፍሰት ውስጥ እየተጠራቀምሽ
ጥልመቱን ድቅድቁን ደንቁርናን ገርሳሽ
እስኪ ልጠይቅሽ እውቀት ተናገሪ
ለመድሽ ወይስ ነሳሽ ዋጥሽ ሳትመረም
በመጠይቅሽ ላይ መጠይቅ ደራርበሽ
በውዝግብ አለም በመንታ መንገድ ላይ ቀጠልሽ እንደዋለልሽ
ወይስ መልስ አገኘሽ ለጥያቄዎችሽ
እስኪ ልጠይቅሽ እውቀት ተናገሪ
ጉዞሽ እንዴት ነበር ቁልቁለት ነው ዳገት
ምን አትርፎ ይሆን እንዲያው ያለፍሽበት
ካለፈው ምን ወሰድሽ ምን ሰጠሽ ለመጪው
እህህ...
እንዲም ነኝ እንዲያም ነኝ የምለውም የለኝ
የሰጡኝን ሁሉ ነሺ ተቀባይ ነኝ
በዘመን ኹረት ውስጥ ሳልጸንስ የማምጥ
ሳልጠይቅ አውቄ ሳልቀድም የምበልጥ
የሆንኩትን ሳልሆን
ያልሆንኩትን የሆንኩ
ሳልወለድ የሞትኩ
ያለስንቅ የተጓዝኩ
ሳልጀምር የደረስኩ
ብከንክን መናኛ ለመሆን ተዳረኩ፤
ግና.....
መናኛ መሆኔ በመቸት ሲለካ
በአንድ አውድ በስዬ ባንዱ አራለው ላካ
በአንዱ ፈክቼ በሌላው ከስማለው
የሆንኩትን ልሆን እንዳልሆንኩ ሆናለው
አንድዜ አበጅጂ አንድዜ እበጃለው
በአንዱ ቤዥቼ በአንዱ እቤዣለው፤
በአንዱ ቃዥቼ በሌላ አልማለው፤
እራሴን በራሴ መዝኜ ባየውም
ፍሬ-ዘርን እንጂ ማብቀያ አይደለሁም
መብቀያዬ ሰው ነው መብሰያዬ እድሜ
የምጓዝ በቀና ስተቴን አርሜ
ለትውልድ የምተርፍ ቀስሜ አቅስሜ
ሲቃና ሰልቼ ሲታመም ታምሜ
ሲፈጥን ሰግሬ ሲደክም አዝግሜ
የተጎዳኘሁኝ በሰው ህላዌ ውስጥ
ሲጠል ሰፍፌ ሲሰምጥ የምዘቅጥ
ባንድ ጎኔ ብስል ባንደኛው ጥሬ ነኝ
ባንደኛው መንገዴ ጪንጫ ይገጥመኛል
መብቀያም ማበቢያም አልሆንሽ ይለኛል
ማለፊያም መድረሻም አልሆንሽ ይለኛል
ቆሞ ቀር ሆኖ ገትሮ ያስቀረኛል
አማትሬ እንዳላይ ገዝፎ ይከልለኛል
ነጭ ቆቡን ደፍቶ ጠቁሮ ይታየኛል
በድንጋይ ላይ በቅሎ ገዝፎ ይታየኛል
አንተ ማነህ ስለው ይሰወርብኛል
ልዳስህም ብልው አልያዝ ይለኛል
ሳይጀምር ጨርሶ ወድቆ ይጥለኛል
የመከሰሬ ሚስጥር የመናኛነቴ
ዋና መገለጫው የድንጋይ ሽበቴ
ልዩ ዋቢነቱም "መራራ ፍሬዬ  መራራ እድገቴ"

*(በቃሉ ሰው መሆን)*

## ለእስር ያላት ብዕር

ከፅንሰት እስከ ልደት፣
ከእድገት እስከ እውቀት፤
ሰብዓዊነት እኩልትን - በመርህ ብትፅፍ፣
ለአንድነት ህብረት - ቆርጣ ብትሰለፍ፣
ሴብነት ጭቆናን - አድሎን ብትፀየፍ፣
ዘረኝነት ልዩነትን - የአንባገነንን ግፍ፤
በሰላም በታገለች፣
አምርራ በሞገተች፣
ዘብጥያ ተጣለች።
ለውይይት ድርድር - የቆረበች ታጋይ፣
ለህዝቦቿ ታማኝ - ቃል ለምድር ሰማይ፤
ስነ-ልቦናዋ - ለትውልድ የሚተርፍ፣
ሰንደቅ ያነገበች - የነፃነት ደጃፍ፣
ለፅኑ ዓላማዋ - ህሊናዋ ማይነጥፍ፣
‹ክልል› ለምኔ - ኢትዮጵያን ብታገዝፍ፤
ቃሊቲ ወረደች፣
ቂሊንጦ ታሰረች፣
ሽብርተኛ ሆነች።
ለእስር ያላት ብዕር - ምታነባ ቀለም፣
ነብስ የማታጠፋ - የማታፈስ ደም፣
የተሰራን ሀገር - ጥላቻ ማታወድም፤
ከስለት ከሹለት - ከመሳሪያም በላይ፣
በህሳብ ንፉጋን - ተፈርታ ምትታይ፤
የሽግግር ሰነድ - አስልታ በከተበች፣
የህገ-መንግስቱን - ጉድለት በነቀሰች፣
አስታራቂ ሀሳብ - ለውይይት ባለች፤
በሀይል ለመናድ - በግድ ተፈርጇ፣
ከወህኒ ቤት ዋለች - በፈሪ ጠመንጃ፣
ፍትህ ተነፈጋት - በስጋት ማስረጃ፣
ወይ የብዕር ፍርጃ፣
መጨረሻዋን እንጃ።



*ርብቃ አብርሐም*
*-ከአውስትራሊያ*

## መልዕክተ ፋኖ ከሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ

ሀገሬ ወልቃይት ወንዙ ወንዛዋንዙ
ሀገሬ አምባማድሪ ወንዙ ወንዛወንዙ
ወይ ሀገሬ ጠለምት ወንዙ ወንዛወንዙ
ያ ሰቲት ሁመራ ወንዙ ወንዛወንዙ
የገነፈለ እለት ብዙነው መዘዙ፡፡
ሀገሬ ማይካድራ በሩ በራብሩ
ሀገሬ ጠገዴ በሩ በራብሩ
ሀገሬ ወገራ ወይ ሀገሬ ስሜን በሩ በራብሩ
እንኳን ጀግና ቆሞ ያስፈራል ግራሩ፡፡
እኔ እወደዋለሁ ጠገዴነቴን
እኔ እወደዋለሁ ጠለምቴነቴን
እኔ እወደዋለሁ ሁመራነቴን
እኔ እወደዋለሁ ኢትዮጵያነቴን
እምነት ከጀግንነት ያስተማረኝን ያስታጠቀኝን፡፡
ማረሻው ምንሽር መጎልጎያው ጎንዴ
የአባ ስበር ሀገር ጎንደር ነው ጠገዴ፡፡
ሀገራችን ጎንደር ወንዛችን ተከዜ
ምን ይመጣብናል እምቢ ባልን ጊዜ፡፡
እንዲህ ጢሶ ጢሶ የነደደ እንደሆን
አመዱን ማፍሰሻ ስፍራው ወዴት ይሆን???
ወገራ አሳላፊ ደንቢያ እንጀራ ጣይ
ተበላህ ጎንደሬ ተበላህ ኢትዮጵያ አትነሳም ወይ???
ሀገሬ ወልቃይት ሀገሬ ሁመራ
ሀገሬ ጠገዴ ወይ ሀገሬ ጠለምት ስሜን አምባራስ
ዋሊያ ያሳድጋል እያበላ ገብስ
ወንድሙን የሚወድ ወገኑን የሚያምነው እንደ ክርስቶስ
ሄደ ገሰገሰ ሀገሩን ሊታደግ ከትህነግ እርሳስ፡፡
አማራው ተነሳ ቁጣው ጋመ ጋለ
ሄደ ወደጠለምት ዘራፍ ጃሎ እያለ
ተመመ ወልቃይት ሀይ ዘራፍ እያለ
ከልጅ መሞት በላይ ከአባት መሞት በላይ ከእናት መሞት በላይ ከሀገር መሞት በላይ ሌላ ምን ሞት አለ???
አንች አትሙችብኝ ኑሪልኝ ኢትዮጵያ ኑሪልኝ ሀገሬ
እኔ አድንሻለሁ እሰዋልሻለሁ ከየትም በርሬ
የተፈጠርኩበት ጎንደር ነው ሀገሬ
የተፈተንኩባት ኢትዮጵያናት ክብሬ



*ውቤ ደነቀው መኮንን*


ኢትዮጵያ ዳግም
የህሊና እስረኞች
ቤት እንድትሆን
መፍቀድ የለብንም!
ባልደራስ
ለእውነተኛ ዲሞክራሲ